# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በውኃ ኃብት ልማት ሚኒስቴር የከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት

## የመስኖ ልማት (Irrigation) ግንባታን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሰኔ 2002

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት ........ 1

የውኃ ሀብት ልማት ሚ/ር ስልጣንና ተግባር ........ 2

የመስኖ ልማት ኘሮጀክቱ አደረጃጀት ........ 3

የመስኖ ልማት ፕሮጀክቱ ዓላማዎች እና የሚጠበቁ ጠቀሜታዎች ........ 4

የመስኖ ልማት ኘሮጀክት የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም፡ ........ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ ........ 5

የኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluation Criteria) ........ 6

የኦዲት ወሰንና ዘዴዎች ........ 6

የስራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 11

የኦዲት ግኝቶች ........ 11

*ሀ. የመስኖ ልማቱ ኘሮጀክት ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ተደርጐ የተጀመረ፣ በተያዘለት ዕቅድ መሠረት የተከናወነ እና የቁጥጥር፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ ........ 11*

የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ዝግጅት ........ 11

የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት (Feasibility study) መደረጉ ........ 12

ግንባታው በአካባቢው ላይ ስለሚያከትለው ተጽእኖ ጥናት መደረጉ ........ 13

የፕሮጀክቱን ስራ እንዲከታተልና እንዲያስተባብር የተቋቋመው ጽ/ቤት በበቂ የሰው ኃይል መደራጀቱ ........ 14

የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ መዘጋጀቱ ........ 15

በፕሮጀክቱ ስራ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች (Risks) የግንባታ ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ መለየታቸው ........ 16

ለመስኖ ልማቱ ግንባታ ዲዛይኖች መዘጋጀታቸው ........ 18

በግንባታ ዲዛይኖቹ ላይ የስኳር ፋብሪካዎቹ አስተያየት እንዲካተት መደረጉ ........ 19

ለግንባታ ስራው የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑ ........ 20

በመስኖ ግንባታ ስራ ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ዝርዝር መረጃ ለፕሮጀክቱ ባለቤት የሚቀርብ መሆኑ ........ 21

የተጠናቀቁ የመስኖ መሬቶች ርክክብ የሚደረግባቸው መሆኑ ........ 22

ለተጠናቀቁ መሬቶች ተገቢው ጥበቃ የሚደረግ መሆኑ ........ 23

ለተሰሩ ስራዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎች በወቅቱ የሚከናወኑ መሆኑ ........ 24

የፕሮጀክቱ ስራ መሪ እቅድ( Master plan) ዝግጅት በጥናት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ........ 25

*ለ. የመስኖ ልማቱ ግንባታ በዕቅዱ መሠረት ተጠናቅቆ ለተያዘለት ዓላማ እንዲውል ለማስቻል የሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋናነት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱ እና ተፈጻሚ መደረጉን ማጣራት ..................................................... 26*

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአፋር ክልል ከተቋቋመው የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር ስላለው የስራ ግንኙነት ......26

የመስኖ ልማቱ ፕሮጀክት በሚሰራበት አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ስለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲጨብጡ መደረጉ..........................................................................................................27

በመስኖ ልማቱ ግንባታ ምክንያት ከይዞታቸው ለሚፈናቀሉ የአካባቢው ኗሪዎች ስለሚከፈለው ካሣ /Compensation/..........................................................................................................28

የግንባታ ስራ ዕቃዎች ከነመጠባቂያ ክምችት (stock) እንዲያዝ ስለመደረጉ .........................................30

ከመስኖ ልማቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ስለሚሰሩ የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ..................................31

**ክፍል ሦስት.......................................................................................................... 32**

የማሻሻያ ሀሳቦች ........................................................................................... 32

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የውሀ ኃብት እና ሰፋፊ በእርሻ ሊሸፈን ከሚችል መሬት ውስጥ ለመስኖ ልማት የዋለው 5 በመቶ ያህሉ ነው፡፡ ይህንን እምቅ ሀብት ጥቅም ላይ ባለማዋልም የአገሪቷ የግብርና ምርት የዝናብ ጥገኛ እንዲሆን በማድረጉ በተለያየ ጊዜ የተከሰተው የድርቅ አደጋ ከፍተኛ ጉዳት ሲያስከትል ቆይቷል፡፡ ይህንን ገጽታ ለመቀየርም በመንግሥት በኩል የተለያየ እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን መንግሥት በዘረጋው የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ፓሊሲ አማካኝነት የመስኖ ልማት ግንባታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡
2. በዚህ መሠረት በውሀ ሀብት ሚኒስቴር የሚከናወነው እና ለመተሃራ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ እንዲሁም በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር በተንዳሆ ለሚቋቋመው አዲስ ስኳር ፋብሪካ ልማት እንዲውል ታቅዶ የከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በ1997 ዓ.ም. ስራ የተጀመረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ፕሮጀክት የሚከናወነው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 471/1998 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ሲውልም በጥቅል የአገሪቷን የስኳር ምርት መጠን በዓመት በ842,937 ቶን ይጨምራል ተብሎ ተገምቷል፡፡ የልማት ስራው የሚከናወነው የአዋሽና የከሰም ወንዝን በመገደብና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የስኳር አገዳ (commercial Sugarcane) ማልማትና አገዳውን ከላይ ለተጠቀሱት ሁለት ፋብሪካዎች በማቅረብ ነው፡፡

## <u>የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት</u>

3. የውኃ ሀብት ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሆኖ በ12 መምሪያዎች እንዲሁም በ7 አገልግሎቶች እና ጽ/ቤቶች የተዋቀረ ሲሆን ከመምሪያዎቹ አንዱ የሆነው የኮንትራት አስተዳደር መምሪያ የመስኖ ልማቱን ግንባታ የመቆጣጠር፣ የመከታተልና የመገምገም ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ይህን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣም ተጠሪነቱ ለመምሪያው የሆነ አንድ የፕሮጀክት አስተባባሪ ቡድን እንዲቋቋምና ለስራው አስፈላጊ በሆነ የሰው ኃይል እንዲደራጅ በመንግሥት ተፈቅዷል፡፡

ከዚህም ሌላ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ ተቋማት ያሉ ሲሆን እነሱም :-

- የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣
- የውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት፣
- ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ኤጀንሲ፣
- የውሃ ሀብት ልማት ፈንድ ኤጀንሲ፣
- የአዋሽ ተፋሰስ ውሃ ሀብት አስተዳደር ኤጀንሲ

ናቸው፡፡

የውሀ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና የውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅቶች በመስኖ ልማቱ ግንባታ በሥራ ተቋራጭነት እና አማካሪ መሐንዲስነት በቅደም ተከተላቸው መሠረት በመሳተፍ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

## የውኃ ሀብት ልማት ሚ/ር ስልጣንና ተግባር

4. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡፡

- ፓሊሲ እና ሕጎችን ያመነጫል፣
- የጥናት ምርምር ተግባሮችን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀናብራል፣ ያሰራጫል፣
- ለክልሎች እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፣ ውሎችንና ዓለምአቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣
- በማቋቋሚያ ሕጎቻቸው ወይም በአዋጅ አንቀጽ 33 ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈፃሚ አካላት አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አደረጃጀታቸውን እንዲሁም የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲቀርቡ ይወስናል፣ ተጠሪ የተደረጉለትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመንግሥት የልማት አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ይቆጣጠራል፣ የልማት አጋዥ ሆነው መሥራታቸውንም ያረጋግጣል፣
- የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የአገሪቱን የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር የውሃ ሀብት አለኝታ በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶች በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፣

- በወሰንና ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ አለምአቀፍ ውሎችን ይደራደራል አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣
- ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት እንዲተላለፉ ካልተደረገ በስተቀር በፌዴራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፣
- የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሥራ በሚገባ መካሄዱን ይቆጣጠራል፣

## <u>የመስኖ ልማት ኘሮጀክቱ አደረጃጀት፣</u>

5. የውሀ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ባለቤት ሲሆን በዋናነት የሚከተሉት ባለድርሻ አካላት (Stakeholders) እንዲሁም በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች አሉ፡-
    - የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር የስኳር ፋብሪካዎቹ ባለቤት፤
    - የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፤ የፕሮጀክቱ ሥራ ተቋራጭ (Contractor)፤
    - የውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት፤ የፕሮጀክቱ አማካሪና ተቆጣጣሪ መሀንዲስ (Consultant)፤
    - የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን፤ በአካባቢው ለሚኖሩ ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች የግጦሽ መሬትና መኖሪያ ቤት ግንባታ የሥራ ተቋራጭ፤
    - የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት፣ የተንዳሆ መስኖ ልማት እርሻ ተረካቢና የመጨረሻ ተጠቃሚ (End user)፤
    - የመተሀራ ስኳር ፋብሪካ፣ የከሰም መስኖ ልማት እርሻ ተረካቢና የመጨረሻ ተጠቃሚ (End user)፤
    - በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዱብቲ ከተማ የሚገኘው የፕሮጀክቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፡- ለመስኖ ልማቱ የእርሻ ቦታ በተከለለው መሬት ላይ የሚገኙትን የአካባቢው ኗሪዎች ወደተዘጋጀላቸው ቦታ ለማንቀሳቀስና የካሳ ክፍያ እንዲያገኙ ለማድረግ፣ ከቦታቸው ለሚፈናቀሉ ኗሪዎች መገልገያ የሚውሉ ማህበራዊ ተቋማት የሚቋቋምባቸው ቦታዎች ለመለየትና የሰፈራ ቦታዎችን ለማዘጋጀት፣ የአካባቢው ኗሪዎች የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እና የመሳሰሉት ኃላፊነቶችን ለመወጣት የተቋቋመ ነው፡፡ ለማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ የስራ ማስኬጃ በጀት የመመደብና ጽ/ቤቱን የማጠናከር ኃላፊነት የተሰጠውም ለውኃ ኃብት ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡

- የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት  ውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ለአካባቢው አርብቶ አደሮች የሚዘጋጀው የግጦሽ መሬት ግንባታ የሥራ ተቋራጭ በመሆን ይሳተፋሉ፡፡

## የመስኖ ልማት ፕሮጀክቱ ዓላማዎች እና የሚጠበቁ ጠቀሜታዎች

6. የመስኖ ልማት ፕሮጀክቱ ዓላማዎች እና የሚጠበቁ ጠቀሜታዎች፦
   - የከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በአገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው የስኳር ምርት ማሳደግ፣ በመስኖ ልማቱ ዙሪያ የሚገኙትን የአካባቢውን አርብቶ አደሮች ሕይወት መለወጥና ማሻሻል፣
   - የስኳር ዕጥረት ማቃለል፣ ስኳር ከውጪ ለማስመጣት የሚወጣውን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ማስቀረትና ከፍጆታ የሚተርፈውን ስኳር ወደ ውጪ በመላክ የውጪ ምንዛሬ ማስገኘት፣
   - በፕሮጀክቱ የግንባታ ሂደት የሚሰማሩትን አገር በቀል የሥራ ተቋራጮችና አማካሪ መሐንዲሶች ክህሎት ማሳደግና ወደፊት የሚታሰቡ ተመሳሳይ ሰፋፊ የመስኖ እርሻ ልማቶች በራስ ኃይል ማከናወን ማስቻል፤ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር የበርካታ ሥራአጥ ወገኖች የኑሮ ሁኔታ መለወጥ፣
   - በአካባቢው  የሚገኘው አርብቶ አደርና አርሶ አደር ህብረተሰብ በመስኖ የታገዘ ምርት እንዲያመርት በማድረግ የምግብ ዋስትናውን ማረጋገጥ፤ የአካባቢውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማሳደግና፣ ተያያዥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መፍጠር፣
   - ሠፊ የመስኖ መሬት በአገዳ ተክል ስለሚሸፈን አገዳው በአካባቢ ያለውን ከፍተኛ የአየር ሙቀት በማስተካከል የአየር ንብረት ሚዛን በመጠበቅ (Eclological Balance) ጠቀሜታ ማስገኘት፣
   - የስኳር አገዳው እና የስኳር ፋብሪካው ተረፈ ምርት ጥቅም ላይ በማዋል በባህላዊ የከብት አርቢነት የተሰማራው የአካባቢው አርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር ኑሮ ወደ ዘመናዊ ከብት አርቢነት ለመለወጥና ከፍተኛ ምርት እንዲያገኝ መርዳት የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## የመስኖ ልማት ኘሮጀክት የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም፡

7. ለከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራ ማከናወኛ በጀት ከመንግስት የተመደበ ሲሆን ከ1998-2001ዓ.ም ብር 416,288,000፣ 389,372,430፣ 528,857,460 እና 580,058,337 በቅደም ተከተል ተመድቧል፡፡ ከዚህም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ብር 427,111,588፣ 407,577,422፣ 522,427,215 እና

578,840,514 ብር ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲገለጽ 102%፣ 104%፣ 98% እና 99.7% በቅደም ተከተል በየዓመቱ ለግንባታ ሥራ መዋሉ በሂሣብ ሪፖርት ተገልጿል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

8. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የውኃ ሀብት ልማት ሚ/ር እያስገነባ የሚገኘውን የከሰም እና ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ተደርጐ የተጀመረ መሆኑና በተያዘለት ዕቅድ መሠረት መከናወኑን፣ የቁጥጥር፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን እና ተፈጻሚ መደረጉን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ዙሪያ የአሠራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡ በዚህ የኦዲት ውጤት የሚቀርቡ የማሻሻያ ሀሳቦች ለተጠቀሰው ፕሮጀክት የተሻለ አፈፃጸም ለማስገኘት ከመርዳቱም በላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደፊት በሚያከናውናቸው የመስኖ ልማት ግንባታ ስራዎች አፈፃፀም የተሻለ እንዲሆን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ

9. ከላይ የተገለፀውን የኦዲት ዓለማ ለማሳካት የመስኖ ልማት ግንባታ ስራውን አፈጻጸም ለመገምገም የሚያስችሉ ሁለት አቢይ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በተራ ቁጥር 1 ለተቀመጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ ሁለት ንዑስ የኦዲት አቅጣጣጫ ተቀምጦለታል፡፡ እነሱም:-

1. የመስኖ ልማቱ ኘሮጀክት ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ተደርጐ የተጀመረ፣ በተያዘለት ዕቅድ መሠረት የተከናወነ እና የቁጥጥር፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣

   1.1 የኘሮጀክቱ ግንባታ ከመጀመሩ አስቀድሞ ተገቢው ቅድመ ዝግጅት የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣

   1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኘሮጀክቱ በተያዘለት ዕቅድ መሠረት መከናወኑን ለመቆጣጠር፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣

2. የመስኖ ልማቱ ግንባታ በዕቅዱ መሠረት ተጠናቅቆ ለተያዘለት ዓላማ እንዲውል ለማስቻል የሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋናነት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን እና ተፈጻሚ መደረጉን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluation Criteria)

10. ለዝርዝር ኦዲቱ ለተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎቹ (Audit Issues) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) የተዘጋጁ ሲሆን የኦዲት መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑ መረጃዎች መካከል የግንባታ ኮንትራት ስምምነት መመሪያ፣ የከሰምና ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የኮንትራት ስምምነቶች፣ የፕሮጀክት መልካም አስተዳደር መርሆዎች (Good project management practices) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ተደርጎ ስምምነት ላይ ተደርሶበታል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪነት ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲት ወሰንና ዘዴዎች

11. ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው የፕሮጀክቱ ግንባታ ሥራ ከተጀመረበት ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 2001 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ የተከናወነውን ሥራ ነው፡፡ በፕሮጀክቱ ስራ የግድብ ግንባታ እና ለመስኖ ልማት የሚውል መሬት ዝግጅትን የሚያካትት ሲሆን በዚህ ኦዲት የታየው ስራ ግን በመስኖ ልማት ግንባታው ላይ በማተኮር ዝርዝር ኦዲቱን ለማከናወን የተመረጡትን የትኩረት አቅጣጫዎች በተመለከተ ከውሀ ኃብት ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት፣ ከውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና ከውሀ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅቶች እንዲሁም ከፕሮጀክቱ ስራ ጋር ግንኙነት ካላቸው በአፋር ክልል ምክር ቤት ስር ከተቋቋመው የፕሮጀክቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና ከመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ጋር ግንኙነት በማድረግ መረጃዎች ተከልሰዋል፡፡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የመስኖ ልማቱ ግንባታ በሚከናወንባቸው ከሰምና ተንዳሆ አካባቢ የግንባታ ሂደቱን በአካል በመገኘት ጉብኝት ተደርጓል፡፡

## 1.2 የስራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

### <u>የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ (Project Proposal):</u>

12. ፕሮጀክቱን ለሚያጸድቀውና በጀቱን ለሚፈቅደው አካል የፕሮጀክት ዝርዝር ጥናት ከመደረጉ አስቀድሞ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ (Project Proposal) መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ይህም ሰነድ ማካተት ካለበት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል፡ የፕሮጀክቱ ዓላማ ምን እንደሆነ፣ ለፕሮጀክቱ መቀረጽ ምክንያት የሆነው ችግር በፕሮጀክቱ እንዴት ሊቀረፍ እንደሚችል የሚያሳይ ሙያዊ ገለፃ፣ ከፕሮጀክቱ የሚገኘው ጥቅም፣ ፕሮጀክቱ የሚወስደው ገንዘብና ጊዜ እና ፕሮጀክቱ የሚፈልገው ባለሙያ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### <u>የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study)</u>

13. የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነዱ ከተዘጋጀ  በኋላ የቅኝት ጥናት (Reconnaissance Study)፣ ቅድመ አዋጭነት ጥናት (Pre-feasibility study) እና ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት (Detail Feasibility study) ይደረጋል፡፡ የአዋጭነት ጥናቱ በፕሮጀክቱ ስራ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ወቅታዊ ሁኔታዎችንና ለወደፊት በስራው ላይ ሊገጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን (Risks) በመለየት ሊወሰዱ የሚገባቸውን የማሻሻያ እርምጃዎች በማወቅ  የፕሮጀክቱ ስራ በሚሰራበት ወቅት ስራ ሳይጓተት በእቅዱ መሰረት ለማጠናቀቅ የሚያስችል ይሆናል፡፡

### <u>አካባቢያዊና ማህበራዊ ጥናት (Social & Environmental Assesement)</u>

14. ፕሮጀክቱ በሚሰራበት ቦታ ያሉትን አካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም በአካባቢው ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖዎች የሚያሳይ  ጥናት ተደርጎ ወደስራ ከመገባቱ አስቀድሞ አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ይደረጋል፡፡

አካባቢያዊ ጥናት ፕሮጀክቱ በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለው ተጽእኖ ሲሆን ማህበራዊ ጥናት ደግሞ ፕሮጀክቱ ለአካባቢው ነዋሪዎች የሚኖረውን ጠቀሜታ እና ጉዳት በተመለከተ እንዲሁም በነዋሪዎቹ የሚኖረውን የተቀባይነት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡

## ባለድርሻ አካላት (Stakeholders)

15. ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ ስራ ላይ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳትፎ ያላቸውና ከስራው ውጤት ተጠቃሚ የሚሆኑ አካላት ናቸው፡፡

በመሆኑም የስራው ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት ከተጠና በኋላ በጥናቱ የተገኙትን ሁኔታዎችና አጠቃላይ ስራውን በሚመለከት ለባለድርሻ አካላት ማሳወቅና እንዲሁም ከስራው ስለሚያገኙት ጥቅምና ስላለባቸው የስራ ኃላፊነትና ግዴታዎች ውይይት በማድረግ ስምምነት ይደረጋል፡፡

## የኮንትራት ስምምነቶች

16. የግንባታና የማማከር ስራ ከሚሰሩ እንዲሁም ሌሎች ስራው ላይ በቀጥታ ከሚሳተፉ አካላት ጋር የኮንትራት ህግን መሰረት ያደረገና ህጋዊ ተፈጻሚነት ያለው ስምምነት ይደረጋል፡፡ በግንባታ ስምምነት መመሪያ መሰረት የግንባታ ኮንትራት ስምምነቶች ሊይዟቸው ከሚገቡ ዋና ዋና ነገሮች መካከል፣ የስምምነቱ አጠቃላይ መግለጫዎች፣ የፕሮጀክቱ ባለቤት ማንነት፣ የግንባታ የዲዛይንና የማማከር ስራ ስለሚሰሩ ድርጅቶች፣ የግንባታ የዲዛይንና የማማከር ስራ የሚሰሩት ድርጅቶች ስላሉዋቸው ሰራተኞች፣ የግንባታ ስራውን የሚሰራው ድርጅት ስላለው የግንባታ እቃዎች፣ ሥራው ስለሚጀመርበትና ስለሚጠናቀቅበት ጊዜ እና የገንዘብ መጠን፣ የዋጋ ልዩነት (Variation) እና ለተጠናቀቁ ስራዎች ስለሚከፈሉ ክፍያዎች፣ ሌሎች ስምምነቱን የሚያደርጉት አካላት የሚኖሩዋቸው ግዴታዎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

## የግንባታ ዲዛይን ዝግጅት

17. በተደረገው ስምምነት መሰረት የግንባታ ዲዛይኑን የሚያዘጋጀው አካል ዲዛይኑን አዘጋጅቶ ካጠናቀቀ በኋላ የፕሮጀክቱ ባለቤት እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በዲዛይኑ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጎ በሰጡት አስተያየት መሰረት ሊሻሻሉ የሚገባቸው ነገሮች እንዲሻሻሉ ይደረጋል፡፡

## የፕሮጀክት የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ ዝግጅት

18. በተደረገው ስምምነት መሰረት የፕሮጀክቱ የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እና ስምምነት ይደረጋል፡፡

ዕቅዱ የሚሰሩትን ስራዎች ዝርዝር፣ ስራዎቹ የሚጀመሩበትንና የሚጠናቀቁበትን ጊዜ፣ የገንዘብ መጠን፣ የሰው ኃይል፣ ማሽኖች እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን የሚያካትት ይሆናል፡፡

## ለአካባቢው ነዋሪዎች የሚከፈል የካሳ ክፍያ

19. የማህበራዊ ጥናቱ ላይ በመመስረት ፕሮጀክቱ በሚሸፍነው አካባቢ የሚገኙና ባለይዞታ ለሆኑ ነዋሪዎች ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ እንዲከፈል እና ሌሎች ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች እንዲሟሉ በማድረግ ቦታው ለስራው ነጻ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## የፕሮጀክቱን ስራ መጀመር

20. በተዘጋጀው የስራ እቅድ መሰረት ወደ ትግበራ ከመገባቱ አስቀድሞ ስራው በተለያዩ ጥሬ እቃዎች እጥረት እንዳይቋረጥ ቢያንስ ዓመታዊ እቅዱን ለማስፈጸም የሚያስችል በቂ ጥሬ እቃ ክምችት (Stock) እንዲያዝ በማድረግ ስራው በእቅዱ መሰረት ይጀመራል፡፡

## ክትትልና ቁጥጥር

21. የክትትልና ቁጥጥር ስራ ለማንኛውም ፕሮጀክት አስፈላጊ ሲሆን የፕሮጀክቱን እቅድ መሰረት የሚያደርግ ነው፡፡ ስራው በተመሳሳይ የጊዜ ልዩነት የሚሰራ ሲሆን በዋናነት የሚሰራው፡ ስራውን ከእቅዱ ጋር በማነጻጸር ያለበትን ደረጃ መመልከት፣ የተጠናቀቁ ስራዎች መጠን፣ የስራው ጥራት በሚፈለገው ደረጃ መሆኑ፣ ለተጠናቀቁ ስራዎች የወጣ አጠቃላይ ወጪ እና በስራው ላይ ስለተሰማሩ ሰራተኞች የስራ ችሎታና የስራ ባህሪ በመገምገም ነው፡፡

## የክንውን ሪፖርት ማቅረብ

22. የስራውን ሂደት በሚመለከት ከስራው ተቆጣጣሪ ድርጅት በየወሩ እንዲሁም የክትትልና ቁጥጥር ስራ ከሚያደርገው አካል (የኮንትራት አስተዳደር መምሪያ) ለስራው ባለቤት ሪፖርት ይቀርባል፡፡ ሁለቱም ሪፖርቶች የሚቀርቡበት የየራሳቸው የተወሰነ ፎርማት ይኖራቸዋል፡፡

## በባለድርሻ አካላት የሚደረግ የፕሮጀክት ክንውን ግምገማ

23. ቁልፍ ባለድርሻ አካላት በየወሩ ስብሰባ በማድረግ የስራውን ሂደት ግምገማ ያደርጋሉ፡፡

## የተጠናቀቁ ስራዎች ርክክብ

24. በየደረጃው የተጠናቀቁና ሸንኮራ አገዳ ለመትከል ዝግጁ የሆኑ መሬቶችን የግንባታና የመሬት ዝግጅቱን የሰራው የኮንስትራክሽን ድርጅት ለፕሮጀክቱ ባለቤት ያስረክባል፡፡ የፕሮጀክቱ

ባለቤትም የተጠናቀቀው በመስኖ የሚለማ መሬት በሚፈለገው ደረጃ የተዘጋጀ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የመሬቱ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች ለሆኑት ለስኳር ፋብሪካዎቹ ያስረክባል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

**ሀ. የመስኖ ልማቱ ፕሮጀክት ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ተደርጐ የተጀመረ፣ በተያዘለት ዕቅድ መሠረት የተከናወነ እና የቁጥጥር፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፣**

**የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ዝግጅትን በተመለከተ**

25. የመስኖ ልማቱ ግንባታ ከመጀመሩ አስቀድሞ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ (Project Proposal) ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች መጽደቅ አለበት፡፡ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነዱም በከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ላይ የተመረኮዘ፣ ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚያሳይና በጥናት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡
26. ይሁን እንጂ ለከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ያልተዘጋጀለት መሆኑ ታውቋል፡፡ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ አለመዘጋጀቱን በውሀ ሀብት ልማት ሚኒስቴር በከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የማህበራዊ ጉዳዮች ተወካይ በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ በቀረበላቸው የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ በሰጡት አስተያየት የገለጹ ሲሆን ከኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስም የፕሮጀክቱ አቀራረጽ ተገቢው የፕሮጀክት ሰነድ ያልተዘጋጀለት በመሆኑ እ.ኤ.አ በ1987 ዓ.ም ለጥጥ እርሻ ልማት ተዘጋጅቶ የነበረውን የአዋጭነት ጥናት መሰረት ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
27. የዚህ ፕሮጀክት ስራ መሰረት ያደረገው የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) የተከናወነው የከሰም ተንዳሆ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ ከ20 ዓመት በፊት (እ.ኤ.አ በ1987 ዓ.ም) በመሆኑ በመስኖ ልማቱ ጅማሮ ወቅት ያለውን የማህበራዊና የአካባቢያዊ ሁኔታዎች የማያመላክት፣ የግንባታ እቃዎች አቅርቦትና የዋጋ ተመን እንዲሁም የጉልበት፣ የነዳጅና ሌሎች ዋጋዎችን፣ ለስኳር ምርት አመቺነትን ወ.ዘ.ተ የማያመላክት በመሆኑ በወቅቱ ውሳኔ ለመስጠትና ተገቢውን ዝግጅት ለማድረግ አያስችልም፡፡ በመሆኑም ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ባለመደረጉ በፕሮጀክቱ የስራ ሂደት ላይ ማጓተት፣ የገንዘብ እጥረት፣ የግንባታ እቃዎች አቅርቦት ችግርና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በተደጋጋሚ ለተከሰቱ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

28. ይህንንም በተመለከተ መውጫ ስብሰባ ላይ ከኃላፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ያልተዘጋጀው የመስኖ ልማት ኘሮጀክቱ በወቅቱ በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረውን የስኳር እጥረት ለመቅረፍ ሲባል በአስቸኳይ እንዲጀመር ከመንግሥት በተሰጠ ውሳኔ መሠረት በመሆኑ እንደሌሎች ኘሮጀክቶች የኘሮጀክት ሥራ ሂደትን (Cycle) በጠበቀ መልኩ የተተገበረ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት (Feasibility study) መደረጉን በተመለከተ</u>

29. የመስኖ ልማቱን ግንባታ አስመልክቶ አካባቢው ለስኳር አገዳ ያለውን ተስማሚነት፣ የግንባታ ማቴሪያሎች ፍላጐትና አቅርቦት፣ የእርሻ መሳሪያዎች ፍላጐት፣ እና አጠቃላይ የታሰበው ፕሮጀክት አዋጪነት (Feasibility study) በዝርዝር ተጠንቶ ለፕሮጀክቱ ባለቤት ሊቀርብና ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

30. በኦዲቱ ወቅት ማወቅ እንደተቻለው ወደ ፕሮጀክቱ ስራ ሲገባ ከ20 ዓመት በፊት ለጥጥ እርሻ ይሆናል ተብሎ የተጠናን ጥናት መሰረት በማድረግ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቱ በተጀመረበት ወቅት አካባቢው ለስኳር አገዳ ልማት ያለውን ተስማሚነት፣ የግንባታ ዕቃዎች ፍላጐትና አቅርቦት፣ የእርሻ መሳሪያዎች ፍላጐት፣ ለፕሮጀክት ስራ ማከናወኛ የሚያስፈልግ የገንዘብ መጠንና የፋይናንስ ምንጭ እና አጠቃላይ የታሰበው የስኳር ልማት አዋጪነት (Feasibility study) አልተጠናም፡፡

31. ከ1998-2000 ዓ.ም አጠቃላይ በውሀ ሀብት ሚኒስቴር አማካኝነት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው እና ከአማካሪ ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ጋር ከተደረገ ቃለ ምልልስ ለመገንዘብ እንደተቻለው ፕሮጀክቱ የተጀመረው በጥድፊያ በመሆኑ የአዋጭነት ጥናት ለማስጠናት ጊዜ እንዳልነበረ እና ለጥጥ እርሻ የተጠናን ጥናት መሰረት ለማድረግ እንደተገደዱ ተገልጿል፡፡

32. ኘሮጀክቱ በተጀመረበት ወቅት የነበሩ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ያመላከተ እና አጠቃላይ የታሰበውን ፕሮጀክት አዋጪነት (Feasibility study) በዝርዝር የሚያሳይ ጥናት አለመጠናቱ ኘሮጀክቱ በምን ያህል ወጪ ሊከናወን እንደሚችል፣ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅና ለግንባታው የሚያስፈልጉ እቃዎች አቅርቦት ባልተጠናበትና ቅድመ ዝግጅት ባልተደረገበት ሁኔታ ስራው እንዲጀመር ተደርጓል፡፡

33. የዚህ ዓይነቱ አካሄድ ላልታሰበ ወጪ የሚዳርግ፣ የተጀመሩ ስራዎች በቅደም ተከተል እንዳይጠናቀቁና በዚህም ምክንያት ለጉዳት የሚያጋልጥ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር እንዳይሰፍንና ለጥፋት የሚዳርግ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አሰራር ሆኖ አልተገኘም፡፡

34. ይህንንም በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ላይ የስራ ኃላፊዎቹ በሰጡት አስተያየት ፕሮጀክቱ መሠረት ያደረገው ከ20 ዓመት በፊት በእንግሊዝና በሩስያ ባለሙያዎች በተጠና የአዋጭነት ጥናትን ሲሆን፣ ይህንን ጥናት በቀጥታ ከመጠቀም በፊት ወቅታዊ ሊደረግ ይገባ እንደነበር ነገር ግን ከነበረው አጣዳፊነት የተነሳ የፕሮጀክቱ ሥራ እንደቀደመ ገልጸዋል፡፡

<u>ግንባታው በአካባቢው ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ጥናት መደረጉን በተመለከተ</u>

35. የመስኖ ልማቱ ግንባታ ከመጀመሩ አስቀድሞ ግንባታው እና የወደፊት የስኳር ልማቱ በአካባቢው ተፈጥሮአዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖና ጠቀሜታ ተጠንቶ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እንዲጸድቅ መደረግ አለበት፡፡

36. የፕሮጀክቱ አካባቢያዊና ማህበራዊ ጥናት በውሀ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት አማካኝነት የተጠና ቢሆንም ጥናቱ ተደርጎ የተጠናቀቀው በ1997 ዓ.ም መጨረሻ ሲሆን የፕሮጀክቱ ስራ የተጀመረው ግን ጥናቱ ከመጠናቀቁ ዘጠኝ ወራት ቀድሞ ነው፡፡ ጥናቱ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ (Environmental impact assessment) በሚል ርዕስ የተዘጋጀና ፕሮጀክቱ በአካባቢው ላይ ሊኖረው የሚችለውን በጎ እና አሉታዊ ተጽዕኖ ያካተተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

37. የመስኖ ልማቱ ግንባታ በአካባቢው ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ የፕሮጀክቱ ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ መጠናት እና ለግንባታ ስራው ግብዓት መሆን ሲገባው ተግባራዊ አለመደረጉ አግባብነት ያለው አሰራር ሆኖ አልተገኘም፡፡

38. የፕሮጀክቱ ግንባታ እና የስኳር ልማት ስራው በአካባቢው ላይ የሚያስከትለውን በጎ እና አሉታዊ ተጽዕኖ በቅድሚያ አለመጠናቱ በተለይ የግንባታ ስራው በአካባቢው ላይ ለሚፈጥረው ማህበራዊም ሆነ አካባቢያዊ ችግሮች በቅድሚያ ዝግጅት እንዳይደረግ አድርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት ለአካባቢው ተፈጥሮአዊ ጉዳዮች (ደን፣ እጽዋት፣ ወንዞች፣ የዱር እንስሳት፣ የእርሻ መሬትና የድንጋይ ማውጣት ስራ፣ አቧራ፣ የተሽከርካሪዎች ድምጽና ሌሎች) በቅድሚያ ዝግጅት አልተደረገባቸውም፡፡ በማህበራዊ ጉዳዮችም በቅድሚያ ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ውይይትና የግንዛቤ ማዳበር ስራ እንዳይሰራ አድርጓል፡፡

39. ይህ አይነቱ ሁኔታ በየሂደቱ ለችግር የሚዳርግ፣ ችግር ከተፈጠረ በኋላም ለማስተካከል በሚደረግ ጥረት ለተጨማሪ ጊዜና ወጪ ከመዳረጉም በተጨማሪ ህብረተሰቡ ሊኖረው የሚገባውን በጎ አስተሳሰብ ሊያዛባ፣ ተፈጥሮአዊ አካባቢን ሊያጎሳቁልና ለብክለት ሊዳርግ፣ የፕሮጀክቱን መጠናቀቂያ ጊዜ በማስተጓጎል ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

40. ይህንንም በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ላይ የስራ ኃላፊዎቹ በሰጡት አስተያየት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (Environmental impact assessment) እና የማህበረሰብ ተጽዕኖ በተመለከተ ኘሮጀክቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ባይሆንም በ1998 ዓ.ም. ከኘሮጀክቱ ሥራ ጋር ጎን ለጎን እንዲጠና መደረጉን ገልጸዋል፡፡

<u>የፕሮጀክቱን ስራ እንዲከታተልና እንዲያስተባብር የተቋቋመው ጽ/ቤት በበቂ የሰው ኃይል መደራጀቱን በተመለከተ</u>

41. ለከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤት የተፈቀደው መዋቅር ዘጠኝ የሰው ኃይል የያዘ ሲሆን እነዚህም የፕሮጀክት አስተባባሪ፣ ፀሐፊ፣ የኮንትራት አስተዳደርና የግንባታ ቡድን መሪ፣ የኮንትራት መሀንዲስ፣ የመስኖ (ሃይድሮሊክ) መሐንዲስ፣ የመስኖ (የውሀ ሀብት) መሀንዲስ፣ ሲቪል መሀንዲስ፣ የማህበራዊ እና የአካባቢ ልማት ትግበራ ቡድን መሪ እና ሶሽዮሎጂስት ሲሆኑ ጽ/ቤቱ በተፈቀደው መዋቅር መሠረት በሰው ኃይል ተሟልቶ ያልተደራጀ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

42. የከሰምና ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤት ተጠሪ ጋር በተደረገ ውይይት እንደተገለጸው ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በተፈቀደው የሰው ኃይል ያልተሟላና በስራ ላይ የሚገኙት ሁለት ባለሙያዎችና አንድ ፀኃፊ ብቻ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ እነዚህም ቢሆኑ ከጥርና ከመጋቢት ወር 2001 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የተመደቡ ሲሆኑ ቀደም ባሉት ጊዜአት ምንም የሰው ኃይል ያልነበረበት ጊዜ እንደነበር ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ጽ/ቤቱ የተሰጠው የስራ ድርሻና ኃላፊነት(duties and responsibiities) በጽሁፍ ያልተዘጋጀና የሰራተኞችም የስራ ድርሻ መዘርዝር (job description) በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. በውሀ ሀብት ልማት ሚ/ር በከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የማህበራዊ ጉዳዮች ተወካይና በሚ/ር መ/ቤቱ የሰው ሀይል መምሪያ ኃላፊ ለኦዲቱ በተዘጋጁ የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ አስተያየት በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት በመዋቅሩ መሰረት በሰው ኃይል ማሟላት አለመቻሉንና ለዚህም ምክንያቱ ለየመደቡ በተመደበው ደሞዝ ሰራተኞችን ለመቅጠር ባለመቻሉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

44. የፕሮጀክቱን ሥራ የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠውና በኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ስር የሚገኘው የከሠም ተንዳሆ መሥኖ ልማት ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በተፈቀደው ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት በሰው ኃይል መደራጀት አለበት፡፡

45. ጽ/ቤቱ በተፈቀደለት መዋቅር መሰረት በሰው ኃይል አለመሟላቱ የሚጠበቅበትን የክትትልና የማስተባበር ስራ በመስራት ኃላፊነቱን እንዳይወጣ አድርጓል፡፡ ለመጥቀስ ያህል በአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት ላይ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ መሆናቸው ክትትል አልተደረገበትም፡፡ በተጨማሪም ጽ/ቤቱ ያለው የስራ ድርሻና ኃላፊነት በጽሁፍ የተገለጸ ባለመሆኑና ለሙያተኞቹም የስራ ድርሻ መዘርዝር አለመዘጋጀቱ የስራ ኃላፊነታቸውን በትክክል እንዳይረዱና ኃላፊነታቸውን እንዳይወጡ ከማድረጉም በተጨማሪ የተጠያቂነት ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ በዚህም ምክንያት ጽ/ቤቱ ምን ያህል ስራውን እንዳከናወነ ለመገምገም አላስቻለም፡፡ ይህ አይነቱ አሰራር ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ስራን ለሰራተኞች ለማከፋፈልና ውጤታማና ስኬታማ መሆኑን ለመከታተል የማያስችል መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

46. በመውጫ ስብሰባ ላይ የስራ ሃላፊዎቹ እንደገለጹት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የፕሮጀክቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ቀድሞ በኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ሥር የነበረ በመሆኑ በወቅቱ የተሟላ የሰው ኃይል እንዳልነበረው፣ በአሁኑ ወቅት ግን የፕሮጀክት ሥራዎች አዲስ በተደራጀ በአንድ የሥራ ሂደት ሥር የተደረገ ሲሆን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባከናወነው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት በሥራ ሂደቱ ውስጥ ያለው የሰው ኃይል የክትትል ሥራውን ለማከናወን በቂ ነው የሚል ዕምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ በተሰጠው መልስ መሠረት የክትትል ሥራው በአግባቡ መከናወኑ እና የሰው ኃይሉ በቂ መሆኑ ወደፊት በመ/ቤታችን በሚደረግ የክትትል ኦዲት የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡

<u>የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያን በተመለከተ</u>

47. በውኃ ሀብት ሚ/ር የከሰምና ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤት የመስኖ ልማት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

48. በውሀ ሀብት ልማት ሚ/ር የከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የማህበራዊ ጉዳዮች ተወካይ በኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ አስተያየት በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት

የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ አለመኖሩንና ለዚህም ምክንያቱ በስራው ላይ የተሳተፉት አማካሪ እና የስራ ተቋራጭ ድርጅቶች የሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል በመሆናቸው የባለቤትነት ስሜት ይኖራቸዋል ተብሎ ስለታሰበ በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል ማኑዋል ያልተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በሚ/ር መ/ቤቱ የከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተጠሪ ጋር በተደረገ ውይይት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

49. የከሰምና ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤት የመስኖ ልማት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ አለበት፡፡

50. መመሪያው አለመዘጋጀቱና ተግባራዊ አለመደረጉ የፕሮጀክቱን የቁጥጥርና ክትትል ስራ ወጥነትና ተቀባይነት ባለው መልኩ እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡ ፕሮጀክቱ የተለያዩ የስራ ዘርፎችን ያካተተ (Multi task) እንደመሆኑ ከዕቅድ ዝግጅት፣ የጊዜ ተመን እና በእያንዳንዱ ዝርዝር ስራ ላይ ለሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር የስራ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ተፈጻሚ አለመደረጉ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

51. የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ዝግጅትን በተመለከተ በኦዲት የመውጫ ስሰባ ላይ የስራ ኃላፊዎቹ እንደገለጹት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ (Manual) ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ይህ መመሪያ በኦዲቱ ወቅትም ሆነ ከዚያ በኋላ ያልቀረበልን እና በየደረጃው ያሉ የሥራ ኃላፊዎች መመሪያው የሌለ መሆኑን ባቀረብንላቸው ቃለ-መጠይቅ ያረጋገጡ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

<u>በፕሮጀክቱ ስራ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች (Risks) የግንባታ ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ መለየታቸውን በተመለከተ</u>

52. መ/ቤቱ የመስኖ ልማት ግንባታው ሂደት ከመጀመሩ በፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን (Risks) በቅድሚያ በማጥናትና በመለየት ሥጋቶቹ እንዳይከሰቱ የሚደረግበት፤ ከተከሰቱም የሚስተካከሉበት፣ የሚወገዱበት፣ የሚቀነሱበት ወይም ወደ ሌላ አካል የሚተላለፉበት (Risk mitigation, avoidance or risk transfer) አማራጮች ማጥናትና መለየት ይኖርበታል፡፡ በጥናቱ የተለዩት አስፈላጊነታቸው የታመነበት የመከላከያና የማስተካከያ ዘዴዎችን በእቅድ ማካተትና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

53. በውሀ ሀብት ልማት ሚ/ር በከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የማህበራዊ ጉዳዮች ተወካይ በኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ አስተያየት በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት ፕሮጀክቱ በአጭር ጊዜ ተጠንስሶ በአጭር ጊዜ እንዲያልቅ በመንግስት በተወሰነው መሰረት በአስቸኳይ የተጀመረ በመሆኑ የቅድሚያ ጥናት እንዳልነበረና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ስትራቴጂ (Risk management strategy) ለመንደፍ በየሳምንቱ የጋራ ስብሰባ እየተደረገ ችግሩን ለማስወገድ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

54. በከሰም መስኖ ልማት ከስራ ተቋራጩ ድርጅት የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እንደገለጹት አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ስራ ሲጀመር የፕሮጀክት ቅርጽ ይዞ ያልተጀመረ በመሆኑ ከሰው ህይወት ጀምሮ ሊደርስ የሚችለውን ችግር ለመከላከልና ለመቋቋም የሚቻልበት ስርዓት አለመዘርጋቱንና እንዲህ አይነት ጥናት በቅድሚያ አለመጠናቱ በዋናው ግድብ ላጋጠመው የመሰረት ግንባታ (Grouting) ችግር መንስኤ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

55. በተንዳሆ ከሚገኙ የአማካሪው እና የሥራ ተቋራጩ ድርጅት ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እንደተገለጸው ሥራው ሲጀመር ዝርዝር ጥናት ያልተደረገ በመሆኑ የስጋት ትንተና አለመዘጋጀቱንና በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቱ በተያዘለት ዕቅድ እንዳይጠናቀቅ ያደረጉ ችግሮች መፈጠራቸውን ገልጸዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በአካባቢው ነዋሪዎች ምክንያት በየጊዜው የተፈጠረው ያለመግባባት ችግር ጉልህ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

56. በመስኖ ልማት ግንባታው ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በቅድሚያ በማጥናትና በመለየት ችግሮቹ እንዳይከሰቱ የሚደረግበት፣ ቢከሰቱም የሚስተካከሉበት፣ የሚወገዱበትና የሚቀነሱበት ወይም ወደ ሌላ አካል የሚተላለፉበት (Risk mitigation, avoidance or risk transfer) አማራጮች በቅድሚያ ተጠንተውና ተለይተው እንዲታወቁ ባለመደረጉ የመከላከያ ቅድመ ዝግጅትም ሆነ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ዘዴዎች አልተነደፉም፡፡ ይህም በመሆኑ ለስጋቶች መከላከያና ማስወገጃ የሚሆን ዕቅድ አለመዘጋጀቱ እና የቅድሚያ ዝግጅት እንዳይኖር አለማደረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

57. በግንባታው ወቅት ከተከሰቱ ችግሮች ለመቀቀስ ያህል በተንዳሆ የፕሮጀክት ስራ ማከናወኛ አካባቢ ከሚኖረው ህብረተሰብ ጋር በተደጋጋሚ በተከሰተው አለመግባባት ሥራ እንዳይሰራ የማስቆም፣ የተሰሩ ስራዎችን የማበላሸት፣ የስራ ማከናወኛ ንብረቶች መጥፋት፣ መስረቅ እንዲሁም በስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ላይ ዘረፋና ድብደባ እንደተፈጸመ ከተደረጉ ቃለ ምልልሶችና ከመ/ቤቱ ሠነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በግንባታ እቃዎች አቅርቦት እጥረት (እንደ ሲሚንቶ፣ ብረት እና የተሸከርካሪ ነዳጅ) ምክንያት የግንባታ ስራው በተያዘለት እቅድ መሰረት እንዳይከናወን ሆኗል፡፡

58. ይህንንም በተመለከተ የስራ ኃላፊዎቹ በመውጫ ስብሰባው ወቅት በተደረገ ውይይት ሊያጋጥም የሚችል ሥጋት (Risk) ቀድሞ ከ20 ዓመታት በፊት በተደረገው ጥናት ላይ በተወሰነ ደረጃ የተቀመጠ ቢሆንም ሥራው ከመጀመሩ በፊት ወቅታዊ የሥጋት ትንተና (Risk assessment) በዝርዝር አለመጠናቱ አንዳንድ ችግሮችን በቅድሚያ በማየት ሥራው ከተጀመረ በኋላ በየጊዜው የሚያጋጥሙ ችግሮች በቅድሚያ በመረዳት የተሻለ መፍትሔ መስጠት እንዳይቻል ማድረጉን፣ ለመጥቀስም ያህል በግንባታ ዕቃዎች የገበያ ዋጋ ያልተጠበቀ የዋጋ ጭማሪ ያጋጠመ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

<u>የመስኖ ልማቱ ግንባታ ሥራ ዲዛይኖች ዝግጅትን በተመለከተ</u>

59. በ1997 ዓ.ም  የመስኖ ልማት ግንባታው ስራ ሲጀመር የፕሮጀክቱ ዲዛይን ዝግጅት እና የግንባታ ሥራው በአንድ ላይ እንዲከናወን የተደረገ (Design under construction) መሆኑን፣ ይህም በመሆኑ ተደጋጋሚ  የዲዛይን ለውጥ እንደነበር እና ሥራዎች በድጋሚ እንዲሰሩ የተደረገበት ሁኔታ የተከሰተ መሆኑ ታውቋል፡፡

60. ይህንንም በተመለከተ በከሰም መስኖ ልማት ፕሮጀክት የውሀ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት የፕሮጀክት ተቆጣጣሪና አማካሪ መሀንዲስ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ በፕሮጀክት ስራ ላይ ተደጋጋሚ የዲዛይን ለውጥ እንዳጋጠመ ለዚህም ዋናው ምክንያት ፕሮጀክቱ ሲጀመር ዲዛይንና ግንባታ በአንድ ላይ እንዲከናወኑ መደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

61. ከውሀ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ ፕሮጀክቱ ሲጠና በድርጅቱ በኩል ታስቦ የነበረው በመጀመሪያ የዲዛይን ክለሳ በማድረግ ወደስራ ለመግባት የነበረ መሆኑን፣ ሆኖም  በስኳር ምርት ላይ እጥረት ስለነበረና አፋጣኝ መፍትሄ በመፈለጉ የዲዛይን ስራው ሳይጠናቀቅ ወደግንባታ እንዲገባ መደረጉንና  በዚህም ምክንያት ችግሮች እንዲከሰቱ አስተዋጽኦ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ከውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ የፕሮጀክት ዲዛይኑ ቀድሞ አለመዘጋጀቱንና፣ ስራው የተጀመረው በሀገራችን ባልተለመደ ሁኔታ የዲዛይንና የግንባታ ስራ በአንድ ላይ መሆኑን (Design under construction) እና የዚህ ዓይነት አካሄድ ለችግር ሊያጋልጥ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

62. በአማካሪ መሐንዲሱ የሚዘጋጁ የመስኖ ልማቱ የግንባታ ዲዛይኖች በነባራዊ የአካባቢው የመሬት አቀማመጥ  ላይ የተመሰረቱ፣ ተደጋጋሚ የዲዛይን ለውጥ የማያስከትሉ እንዲሆኑ፣ ዲዛይኑ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት  መረጋገጥ ነበረበት፡፡

63. ለከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ግንባታ ስራ በቅድሚያ የዲዛይን ጥናትና ተጓዳኝ ዝግጅት አለመደረጉ ለተጨማሪ ወጪ እና የጊዜ መራዘም የዳረገና፣ የስኳር አቅርቦቱንም በታሰበለት ጊዜ ለገበያ ለማቅረብ አለማስቻሉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለአንድ የመስኖ ልማት ግንባታ በቅድሚያ ዲዛይን እንዲዘጋጅ አለመደረጉ ተጠያቂነትን በማስፈን ሂደት እንዲሁም በቁጥጥር ስራዎች ላይ ክፍተት የሚፈጥር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

64. ይህንንም በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ከሥራ ኃላፊዎቹ ጋር በተደረገው ውይይት የፕሮጀክት ዲዛይን በቅድሚያ አለመሰራቱ ከተለመደው የፕሮጀክት አሰራር ሥርዓት አንፃር ትክክል ባይሆንም ከላይ እንደተገለፀው ከመንግሥት በተሰጠ ውሳኔ አዲስ የአተገባበር ሥልትን በመከተል ኢንጂነሪንግ፣ ግዥ እና ግንባታን (Engineering procurement and construction) በተጓዳኝ ማከናወን በሚለው መርህ በፍጥነት የተጀመረ በመሆኑ የተከሰተ ሁኔታ መሆኑን፤ በዚህ ሁኔታ መጀመሩ ደካማም ጠንካራም ጎኖች እንደነበሩት፤ ጠንካራ ጎኑ በሀገሪቱ እየጎላ የመጣውን የስኳር አቅርቦት ችግር በፍጥነት ለመፍታት የሚረዳ መሆኑ ሲሆን፣ ደካማ ጎኑ ደግሞ ሥራው በፍጥነት ከመጀመሩ የተነሳ ያለበቂ ጥናትና ቅድመ ዝግጅት በመጀመሩ ከፍተኛ ገንዘብ መጠየቁ እና ማህበራዊውን ችግር ለመፍታት አለመቻሉ እንደሆነ፤ በጥቅሉ ሲታይ ግን ከዚህ ፕሮጀክት ትልቅ ትምህርት አግኝተንበታል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

<u>በግንባታ ሥራ ዲዛይኖች ዝግጅት ላይ የስኳር ፋብሪካዎች አስተያየት መካተትን በተመለከተ</u>

65. በመስኖ ልማት ግንባታ ዲዛይን ዝግጅት ላይ የመስኖ ልማቱ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች (የስኳር ፋብሪካዎች) አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጎ አስተያየታቸው እንዲካተት መደረግ ይኖርበታል፡፡

66. በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው በፕሮጀክቱ ስራ ላይ ተሳትፎ ሊኖራቸው የሚገባ ባለድርሻ አካላት ወይም የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች የሆኑት የስኳር ፋብሪካዎች በእቅዱም ሆነ በግንባታ ዲዛይኑ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ያልተደረገ መሆኑና በዚህም ምክንያት አንዳንድ ሥራዎች በድጋሚ እንዲሰሩ የተደረገበት ሁኔታ እንደነበር ታውቋል፡፡ ለምሳሌ ያህልም በከሰም ለ24 ሰዓት ሊያጠጣ የሚችል የመስኖ ስራ ተሰርቶ የነበረ ቢሆንም ሥራው በመተሀራ ስኳር ፋብሪካ ተቀባይነት ባለማግኘቱ በድጋሚ ፈርሶ ለ12 ሰዓት ሊያጠጣ እንዲችል ተደርጎ ተሰርቷል፡፡ ለዚህም ተጨማሪ ስራ የወጣን ወጪ (ተጨማሪ ጊዜና ሌሎች ወጪዎችን ሳይጨምር ቀጥተኛ የሆነ ወጪ ብቻ)ብር 700,000 ሺህ መሆኑን ከመረጃዎች ለመመልከት ተችሏል፡፡

67. ይህንንም በተመለከተ በከሰምና ተንዳሆ ካሉ የአማካሪውና የተቋራጩ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ የስኳር ፋብሪካዎቹ እየተዘጋጀ በነበረው ዲዛይን ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ከመተሀራ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት ምርታማነት ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ ቀድሞ ፕሮጀክቱ ሲታሰብ አዲስ ለሚቋቋመው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የነበረ በመሆኑና የመተሀራ ስኳር ፋብሪካን ታሳቢ ያላደረገ ስለነበር በዲዛይኑ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አለመደረጉን ገልፀዋል፡፡

68. ለመስኖ ልማት ግንባታው በየደረጃው በሚዘጋጀው ዲዛይን ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ያልተደረገ መሆኑ በፕሮጀክቱ ስራ ላይ ተጨማሪ ጊዜና ወጪ ከማስከተሉም ባሻገር ፋብሪካዎቹ የቅድሚያ ዝግጅት እንዳያደርጉ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

69. በኦዲት የመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገው ውይይት ፕሮጀክቱን የሚረከቡ የስኳር ፋብሪካዎች ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት የፕሮጀክቱ ንድፍ (Design) ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት አለመደረጉ የተለመደውን የፕሮጀክት አተገባበር የተከተለ ባይሆንም ሥራው ከተጀመረ በኋላ ተሳትፎ ያደረጉባቸው ሁኔታዎች የነበሩ መሆኑን፣ በተለይ የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ አሁንም ብዙ ተሳትፎ እያደረገ እንደሚገኝ በስራ ኃላፊዎቹ ተገልጿል፡፡

<u>የግንባታ ስራው ወርሃዊ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅትን በተመከተ</u>

70. የፕሮጀክቱን ስራ በተመለከተ በየወሩ በሥራ ተቋራጩ እየተዘጋጁ በአማካሪ መሐንዲሱ አማካኝነት ለውሀ ሀብት ሚ/ር የሚቀርቡ የስራ ክንውን ሪፖርቶች ላይ ለወሩ በዕቅድ የተያዘው (Planned) እና በሥራ ላይ የዋለው (Actual) የሰው ኃይል፣ ማሽኖች እና የግንባታ ቁሳቁሶች ሊካተቱ ይገባል፡፡

71. በ1999፣ 2000 እና 2001 ዓ.ም በተዘጋጁ የግንባታ ሥራው ወርሀዊ ሪፖርቶች ላይ እንደተመለከትነው በየወሩ በዕቅድ የተያዘው እና በስራ ላይ የዋለ ማሽን በንጽጽር እየተዘጋጀ የሚቀርብ ቢሆንም የሰው ሀይል አጠቃቀምን በተመለከተ በእቅድ የተያዘው ሳያካትት በስራ ላይ የዋለው ብቻ በሪፖርቱ የሚቀርብ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

72. ይህንንም በተመለከተ በከሰምና ተንዳሆ ከሚገኙ የአማካሪ ድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ በየወሩ እየተዘጋጀ በሚቀርበው የእቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ በዕቅድ የተያዘው የሰው ኃይል ስራ ላይ ከዋለው ጋር በንጽጽር እንደማይቀርብ፣ ለዚህም ምክንያቱ ዝርዝር ዕቅዱ ሚ/ር መ/ቤቱም ጋር ያለ በመሆኑ ንጽጽሩን እዛው መስራት ስለሚቻል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

73. የዚህ አይነት ሪፖርት አቀራረብ ለወሩ ሥራ የታቀደው የሰው ኃይል ሥራ ላይ ከዋለው የሰው ሀይል ጋር ለማነጻጸር የማያስችል በመሆኑ የተሰሩ ስራዎች ለሥራው በሚመጥን የሰው ሀይል መሰራታቸውን ለማረጋገጥ እና ለመከታተል የማያስችል፣ በየጊዜው ለሚከሰት የሰው ሀይል እጥረትም መፍትሄ ለመፈለግና እርምጃ ለመውሰድ የሚያዳግት ከመሆኑም ባሻገር ሥራው በኮንትራት ስምምነቱ መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ የማያስችል እና የተጠያቂነት ስርዓትን የማያጠናክር መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

74. ይህንንም በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የሰው ኃይልና ማሽነሪን በተመለከተ ቀድሞ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ስምምነት የተደረገበት ከመሆኑም በላይ ድርጅቶቹ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑ እና በቅርብም ያላቸው መዛሪያዎች እና የሰው ኃይል በሚኒስቴሩ የሚታወቅ በመሆኑ በየወሩ ሪፖርት የማቅረቡ ጠቀሜታ እንዳልታመነበት ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ይህ አባባል ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የማያስችል በመሆኑ አሰራሩ ሊስተካከል ይገባል፡፡

<u>በመስኖ ግንባታ ስራ ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ዝርዝር መረጃ ለፕሮጀክቱ ባለቤት የሚቀርብ መሆኑን በተመለከተ</u>

75. የውሀ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት የከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ግንባታን በተመለከተ የገባውን ግዴታ ለመወጣት ይችል ዘንድ በመስኖ ልማቱ ስራ ላይ አገልግሎት እንዲሰጡ የመደባቸውን ሠራተኞች ዝርዝር ሁኔታ (Biographical data) የሚገልጽ ሰነድ በማዘጋጀት ለውሀ ሀብት ሚ/ር በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

76. ይህንንም በተመለከተ በውሀ ኃብት ሚ/ር የኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ እና በከሰም የአማካሪው ድርጅት ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ በግንባታ ስራው ላይ የተሳተፉት የስራ ተቋራጩ እና የአማካሪ ድርጅቱ በውኃ ኃብት ሚ/ር ውስጥ እንደሚገኙ የስራ ክፍሎች የሚታዩ በመሆናቸው የሰራተኞች ዝርዝር መረጃ ለሚ/ር መ/ቤቱ እንዲልኩ እንደማይደረግ ተገልጿል፡፡

77. በውሀ ሀብት ሚ/ር እና በአማካሪ ድርጅቱ መካከል በተደረገው ውል መሰረት በፕሮጀክቱ ስራ ላይ የሚመደቡ የአማካሪ ድርጅቱ ሰራተኞች ዝርዝር ሁኔታ ለፕሮጀክቱ ባለቤት በጽሁፍ ማሳወቅ እንዳለበት የተገለፀ ሆኖ ሳለ አማካሪ ድርጅቱ በውሉ ላይ የተገለጸውን ግዴታ ተፈጻሚ አለማድረጉ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ ስምምነት የተደረገውም ውል ሰጪና ውል ተቀባይ የየበኩላቸውን ግዴታ ለመወጣት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በስምምነቱ መሠረት ተፈጻሚ ባለመሆኑ የፕሮጀክቱ ግንባታ ስራ ተገቢው ችሎታና ብቃት ባለው የሰው ኃይል ክትትልና ቁጥጥር የተደረገበት መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

## የተጠናቀቁ የመስኖ መሬቶች ርክክብን በተመለከተ

78. በየደረጃው የዝግጅት ስራቸው የሚጠናቀቅ የመስኖ ልማት መሬቶች ርክክብ መፈፀም ያለበት በውሃ ሀብት ሚ/ር እና በውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል መሆን ይኖርበታል፡፡

79. በከሰም የአማካሪ ድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እንደተገለጸው የተወሰነ መሬት የመተሀራ ስኳር ፋብሪካ እንዲረከበው ተደርጎ የሸንኮራ አገዳ እየለማበት ሲሆን ርክክቡ ግን የኮንስትራክሽን ስምምነቱን የተከተለ እንዳልነበረ፣ ርክክብ ሲደረግም የተዘጋጀ የርክክብ ሰነድ ያልነበረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህ የተደረገው ሁሉም በፕሮጀክቱ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የመንግስት መ/ቤቶች በመሆናቸው እና ለስራው መፍጠን ብቻ ስለሚታሰብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

80. በተንዳሆ የአማካሪ ድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ርክክቡ በውሉ የተገለጸውን ስርዓት የጠበቀ እንዳልነበረና የተረካከቡበት ማስረጃም እንዳልተዘጋጀ፣ የፕሮጀክቱ ባለቤት የውሀ ኃብት ሚ/ርም በደብዳቤ ባይሆንም ሁኔታውን እንዲያውቅ በስብሰባ መገለጹን አብራርተዋል፡፡

81. ከመተሀራ ስኳር ፋብሪካ የፕሮጀክት ምርታማነት ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ስለመስኖ ልማት መሬት ርክክብ ስምምነት አለመደረጉን፣ እስካሁንም የተረከቡት ከአማካሪ ድርጅቱ ላይ መሆኑንና ለርክክቡም የመረካከቢያ ሰነድ አለመዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

82. የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ የመስኖ መሬቶች በየደረጃው የሥራ ተቋራጩ ለውሀ ሀብት ሚ/ር ማስረከብ እንዳለበት በውሉ የተገለጸ ቢሆንም ርክክብ ተፈጽሞ የተገኘው ግን በውሉ መሰረት ሳይሆን ከውሉ ውጭ የስራ ተቋራጩ ለመተሀራ ስኳር ፋብሪካ ያስረከበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

83. ይህ አይነቱ የርክክብ ስርዓት በመ/ቤቶቹ መካከል የተደረገውን የኮንትራት ስምምነት መሰረት ያላደረገ፣ የተጠያቂነት መርህን ያልተከተለ፣ ለመስኖ ልማት መሬት የተዘጋጀውና ርክክብ የተደረገበት መሬትም በውሉ መሰረት ደረጃውን ያልጠበቀ ሆኖ ቢገኝ ለስራ መቆምና ላልታሰበ ችግር የሚዳርግ መሆኑ ግንዛቤ ያልተወሰደበት አካሄድ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው አሰራር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ርክክብ የተደረገባቸው የመስኖ መሬቶች በውሉ መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በተፈለገው ጊዜ ውስጥ የተዘጋጁና መጠናቸው ምን ያህል እንደሆነ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

84. ይህንንም በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ከኃላፊዎች ጋር በተደረገ ውይይት ርክክብን በሚመለከት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተረክቦ ለተጠቃሚዎቹ ማስረከብ የነበረበት ቢሆንም በዚህ መልኩ አለመተግበሩ ትክክል አለመሆኑን፣ በዚሁ አካሄድም ችግሮች እየተፈጠረ መሆኑን፣ ለመጠቀስም የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ አንዳንድ ጊዜ አልረከብም የሚልበት ሁኔታ በመከሰቱ ሥራ ላይ ሊውል የሚገባው መሬት ሌላ ነገር እየበቀለበት እንደገና ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግበት ሁኔታ መታየቱን ገልጸዋል፡፡

## ለተጠናቀቁ የመስኖ መሬቶች ተገቢው ጥበቃ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ

85. ደረጃ በደረጃ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማቱ የግንባታ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ርክክብ እስኪደረግባቸው ድረስ ለብልሽት እንዳይዳረጉ በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (ተቋራጩ) አማካኝነት ተገቢው ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ የመስኖ ልማቱ መሬቶች ርክክብ እስኪደረግባቸው ድረስ የሚደረገው የጥበቃ ስርዓት  ያልተጠናከረና የተሰራውን ስራ ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅትና ከፕሮጀክቱ የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

87. ከተንዳሆ የስራ ተቋራጩ ድርጅት ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ብዛታቸው 900 የሆነ የጥበቃ ሰራተኞች ቢኖሩም በተለያዩ ሰዎች የሚደርሰውን ችግር ለመከላከል አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

88. ከአማካሪ ድርጅቱ ለውሀ ሀብት ሚ/ር በየጊዜው በተጻፉ የተለያዩ ደብዳቤዎች ላይ ለመመልከት እንደተቻለው ከአካባቢው ነዋሪዎች ተውጣጥተው የተቀጠሩ የጥበቃ ሰራተኞች በአግባቡ በስራቸው ላይ የማይገኙ በመሆናቸው የስራ መበላሸትና የንብረት መሰረቅ ችግር እያጋጠመ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡

89. በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ እንደተቻለው የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት መሬቶች ላይ ለሚደረገው ጥበቃ ሰራተኞች የተመደቡለት ቢሆንም የቁጥጥርና የክትትል እንዲሁም የቅኝት (Patrol) ስራዎች የማይከናወኑ መሆኑን ነው፡፡ ሁኔታው የመንግስት ሀብትና ንብረትን ለጥፋት የሚዳርግ በመሆኑ በአስቸኳይ ሊታረም ይገባል፡፡

__ለተሰሩ ስራዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎች በወቅቱ የሚከናወኑ ስለመሆኑ__

90. ከ2001 ዓ.ም እስከ 2002 ህዳር ወር ድረስ የተጠየቁትን የክፍያ ጥያቄዎች (payment certificate) እንደ ናሙና በመጠቀም ከታዩት 12 የክፍያ ጥያቄዎች መካከል 7ቱ (58.3%) ከ28 ቀናት በላይ የዘገዩ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የክፍያ ጥያቄዎችም ከ28 ቀናት በላይ የዘገዩበት ጊዜ ከፍተኛው 29 ቀናት ሲሆን ዝቅተኛው 2 ቀናትነው፡፡ ይህም ክፍያዎች በአማካይ 16 ቀናት የሚዘገዩ መሆኑን በትንተናው ለማየት ተችሏል፡፡ ክፍያዎቹ የሚዘገዩት አማካሪው ድርጅቱ ጋ ለማጣራት መሆኑን መረጃዎች ቢያሳዩም የፕሮጀክቱ ባለቤት ጋም የሚቆዩበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

91. ይህንንም በተመለከተ በተንዳሆ የስራ ተቋራጩ ድርጅት ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ክፍያ ከ 28 ቀናት በላይ የሚቆይ መሆኑንና ይህም የሚሆነው አማካሪ ድርጅቱ ጋ እና የፕሮጀክቱ ባለቤት ጋ የሚቆይ በመሆኑ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

92. በስራ ተቋራጩ ተዘጋጅተው እና በአማካሪ መሐንዲሱ ፀድቀው ለፕሮጀክቱ ባለቤት የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎች (payment certificates) ለተከናወኑ ሥራዎች መሆኑ በወቅቱ ተረጋግጦ ክፍያው በ28 ቀናት ውስጥ መከፈል ይኖርበታል፡፡

93. ለተሰሩ ስራዎች ክፍያ በስምምነቱ መሠረት በወቅቱ አለመፈጸሙ ስራው በሚፈለገው ጊዜ እንዳይጠናቀቅ፣ በተገቢው ቅልጥፍና እንዳይካሄድ የራሱ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መታወቅ ይኖርበታል፡፡

## የፕሮጀክቱ ስራ መሪ እቅድ (Master plan) ዝግጅት በጥናት ላይ የተመሰረተ መሆኑን በተመለከተ

94. የመስኖ ልማት መሬት ዝግጅት እና የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት አለበት፡፡

95. ፕሮጀክቱ የተጀመረው በ1997 ዓ.ም ሲሆን የመጀመሪያው መሪ ዕቅድ (Master plan) ጸድቆ ሲሰራበት የቆየ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት መሄድ ስላልተቻለ ክለሳ ተደርጎበት በ1999 ዓ.ም. እንደገና መሪ ዕቅድ “B” (Master plan "B") በሚል ተዘጋጅቶ ጸድቋል፡፡ ይህም መሪ ዕቅድ አሁን ካለው ስራ ጋር እየተጣጣመ መሄድ ስላልቻለ በአሁኑ ወቅት ሌላ መሪ ዕቅድ እየተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

96. በመሪ ዕቅድ “B” መሰረት የመስኖ መሬት ዝግጅት ስራው (Irrigation) እና የአገዳ ተከላው (Sugarcane planting) ስራ እስከ 2012 እንደሚጠናቀቅና በየዓመቱ በተንዳሆ 12,500 ሄክታር ለማልማት ቢታቀድም ከተንዳሆ የስራ ተቋራጩ ድርጅት ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እስከ 2009 ዓ.ም. የለማው የመሬት መጠን 6000 ሄክታር ብቻ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

97. ከውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ስራው እየተከናወነ ያለው በመሪ ዕቅድ “B” መሰረት ሲሆን በዚህ ዕቅድ መሠረት የመስኖ ልማቱ ስራ እ.ኤ.አ በ2012 ይጠናቀቃል ተብሎ የተያዘ ቢሆንም በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ተከላ መጓተት ምክንያት ዕቅዱን ተፈጻሚ ማድረግ እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

98. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እንደተገለጸው የፕሮጀክቱ ስራ በይፋ የተጀመረው በ1997 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ 2004ዓ.ም) ሲሆን ፕሮጀክቱ ሲጀመር በእቅድ የተያዘው እስከ 2001 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ 2008 ዓ.ም) ድረስ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

99. ዕቅድን ከነባራዊ ሆኔታዎች ጋር ለማጣጣም የክለሳ ስራ አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ ሆኖም በአምስት ዓመት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ለታቀደ ፕሮጀክት ክለሳ ተደርጎበት የተዘጋጀ መሪ ዕቅድ እንደገና ሁለት ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ለአገልግሎት ሊውል አለመቻሉ ዝግጅቱ በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

## ለ. የመስኖ ልማቱ ግንባታ በዕቅዱ መሠረት ተጠናቅቆ ለተያዘለት ዓላማ እንዲውል ለማስቻል የሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋናነት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱ እና ተፈጻሚ መደረጉን በተመለከተ

### ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአፋር ክልል ከተቋቋመው የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት በተመለከተ

100. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር የከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራን ለማስተባበር የተቋቋመው ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ያለውን የስራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት በዝርዝር፣ በጽሁፍ ሊገለጽ ይገባል፡፡

101. ሆኖም ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ያለው የስራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የሚኖረው የስራ ግንኙነት በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ያልተሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

102. ይህንንም በተመለከተ በአፋር ክልል ለፕሮጀክቱ አስተባባሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በተሰጠው መልስ የጽ/ቤቱ የስራ ድርሻና ዝርዝር ኃላፊነቱ በጽሁፍ ያልተዘጋጀው የተቋቋመበት ዓላማ የታወቀ በመሆኑ ሁሉም ይገነዘበዋል በሚል ግምት እንደሆነ፣ የጽ/ቤቱም ዓላማ የአካባቢውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ ማድረግና በፕሮጀክቱና በህብረተሰቡ መካከል ቀና ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ እንደሆነም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

103. የዚህ ዓይነቱ አሰራር የስራ እቅድ ከማዘጋጀት፣ ኃላፊነትን በእቅድ ተፈጻሚ ከማድረግ፣ የስራ አፈጻጸምን ከመከታተልና ስኬታማ ከመሆን እንዲሁም ተጠያቂነት ከማጠናከር አኳያ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

104. በመሆኑም ጽ/ቤቱ በፕሮጀክቱ የማስተባበር ስራ ላይ የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣቱን ለማረጋገጥ እና የስራ አፈጻጸሙን ኦዲት ለማድረግ አላስቻለም፡፡ ጽ/ቤቱ 14 ሞያተኞችን የሚይዝ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲኖረው ተደርጎ የተቋቋመ ሆኖ ሳለ በሶስት የሰው ኃይል የሚንቀሳቀስ ሆኖ ለመገኘቱም አስተዋጽኦ ያደረገው አንዱ ምክንያት ዝርዝር የስራ ኃላፊነት ያለመታወቅ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ጽ/ቤቱም በተፈቀደለት ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት የሰው ኃይሉን አሟልቶ በአግባቡ ስራን ባለማከናወኑ ምክንያት በተንዳሆ መስኖና ግድብ የግንባታ ስራዎች ላይ በየጊዜው የተከሰተውን ማህበራዊ ችግር እልባት ላይ ለማድረስ አለመቻሉ አንዱ ተጠቃሽ ጉዳይ ነው፡፡

105. ይህንንም በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ወቀት በተደረገ ውይይት በአፋር ክልል ከተቋቋመው የማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ በቂ ውይይት ተደርጎበትና የሥራ

ድርሻ ክፍፍል እንዲኖር ተደርጎ የተጀመረ መሆኑንና ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ይህ የመስኖ ኘሮጀክት በተጀመረበት ወቅት መንግሥት የክልሉ መንግሥት እገዛ ሊያደርግ ይገባል በማለቱ ገለልተኛ (Independent) ሆኖ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በተወሰነ ደረጃ ማለትም በተሽከርካሪና መጠነኛ የበጀት ድጎማ ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን የስራ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም የተሰጠው መልስ ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ሙሉ ለሙሉ ሊቀርፍ የሚችል ባለመሆኑ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ያለው የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የሚኖረው የሥራ ግንኙነት በዝርዝር በጽሁፍ ሊገለጽ ይገባል፡፡

<u>የመስኖ ልማቱ ፕሮጀክት በሚሰራበት አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ስለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንደኖራቸው የተደረገ መሆኑን በተመለከተ</u>

106. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና ሌሎች የመስኖ ልማቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በመስኖ ልማቱ አካባቢ ሰፍሮ የሚገኘው ህብረተሰብ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት ስለ መስኖ ልማቱ ጠቀሜታና ከህብረተሰቡ ስለሚጠበቅ ትብብር በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይት ሊደረግ ይገባል፡፡ ሕብረተሰቡም በመስኖ ልማቱ ላይ የባለቤትነት፣ የተባባሪነት እና የተቆርቋሪነት ስሜት እንዲያጎለብት የኘሮጀክቱ የግንበታ ሥራ ከመጀመሩ በፊት እና በሂደትም በየጊዜው የሚደረግ የውይይት መርሐ ግብር መዘጋጀትና ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

107. በውሀ ሀብት ሚኒስቴር የኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ፕሮጀክቱ በበቂ ጥናት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ የአካባቢው ህብረተሰብ በፕሮጀክቱ የሚያገኘው ጥቅም እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ መውሰድ ስላለበት እርምጃ በቀድሞ ጥናት አለመካተቱ ለችግሩ መከሰት ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

108. በከሰም የስራ ተቋራጩ ድርጅት ኃላፊ እና በተንዳሆ ከአማካሪው ድርጅት ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እንደተገለጸው ችግሩ የፕሮጀክቱ ስራ ከመጀመሩ በፊት ህብረተሰቡ ስለኘሮጀክቱ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ባለመደረጉ በተለይ ሥራው በተጀመረ የመጀመሪያ 2 እና 3 ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ ያለመግባባትና ያለመተባበር ችግር መከሰቱን ገልጸዋል፡፡ በአብዛኛው ችግሩ የሚከሰተው አግባብ ያልሆነ የቅጠሩን ጥያቄ ከህብረተሰቡ የሚነሳ በመሆኑና ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ እንደሆነም ጨምረው አብራርተዋል፡፡

109. በአፋር ክልል ከሚገኘው የፕሮጀክቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር በተደረገ ውይይት እንደተገለጸው ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት ህብረተሰቡ ስለስራው በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ያልተደረገ በመሆኑ ችግሮች ተከስተው እንደነበር፣ በአሁኑ ወቅት ግን ችግሩ የሚከሰተው ህብረተሰቡ ስለስራው ግንዛቤ ስለሌለው ሳይሆን ከግል ጥቅም ጋር በተያያዘ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ህብረተሰቡ በራሱ የሸንኮራ አገዳ በመትከል ተጠቃሚ እንደሚሆን የተገለጸለት ቢሆንም ለህብረተሰቡ የተባለው መሬት ተለይቶ ባለመዘጋጀቱና እንዲታወቅ ባለመደረጉ ቅሬታ መኖሩን፣በልዩ ልዩ ዘርፍ ስልጠና ያገኙ የአካባቢው ነዋሪዎች የስራ ዕድል የሚገኝበት ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ አሁን ላሉት ማህበራዊ ችግሮች መከሰት የሚጠቀሱ ምክንያቶች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

110. የከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት የግንባታ ስራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ህብረተሰብ ከመኖሪያ ስፍራው፣ ከእርሻውም ሆነ ከግጦሽ መሬቱ ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ ሳለ ስለ ማህበራዊ ጉዳይ በቅድሚያ ጥናት አለመደረጉ በሂደትም በየደረጃው አፋጣኝ ጥናት በማድረግ ከህብረተሰቡ ጋር ውይይት አለመደረጉ የፕሮጀክት ስራ መርህን የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡

111. በመስኖ ልማቱ አካባቢ ሰፍሮ ለሚገኘው ሕብረተሰብ ስለ መስኖ ልማቱ ጥቅም በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ አለመደረጉ ነዋሪዎቹ በስራው የባለቤትነት ስሜት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ በመሆኑ ችግር የሚያስከትል እና በሚፈጠረው ማህበራዊ ችግር ምክንያት ስራው በእቅዱ መሰረት እንዳይከናወን የሚያደርግ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰቡ የልማት ፕሮጀክቶችን በበጎ መልኩ ሊመለከት የሚችልበትን አጋጣሚ በማተስንጎል በሌሎች ፕሮጀክች ላይ ተመሳሳይ ችግር እንዲፈጠር መንገድ የሚከፍት ይሆናል፡፡

112. ይህንንም በተመለከተ በመውጫ ስብሰባው ወቅት ከሥራ ኃላፊዎቹ ጋር በተደረገው ውይይት በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር ፕሮጀክቱ በተጀመረበት ወቅት በቂ ውይይት ተደርጎ ከክልል መስተዳድሩ ጀምሮ ፕሮጀክቱ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ግን እነርሱ ጥጥና ሰሊጥ የሚያመርቱበት አካባቢ ስለነበረ የአካባቢው ህብረተሰብ ጥቅሜ ይነካብኛል በሚል ምክንያት ፕሮጀክቱን እናውቀውም ማለት የጀመሩበት ሁኔታ መከሰቱን ገልፀዋል፡፡

## በመስኖ ልማቱ ግንባታ ምክንያት ከይዞታቸው ለሚፈናቀሉ የአካባቢው ኗሪዎች የሚከፈለውን ካሣ /Compensation/ በተመለከተ

113. ለመስኖ ልማት በሚውለው ስፍራ ለሚገኙ እና በዚሁ ግንባታ ምክንያት ከቦታቸው ለሚፈናቀሉ የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲከፈል በመንግሥት የተፈቀደው ካሣ /Compensation/ የፕሮጀክቱ ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊከፈልና ቦታው ለተፈለገው ሥራ ነፃ ሊደረግ ይገባል፡፡

114. በ1999ዓ.ም በተዘጋጀው የፕሮጀክቱ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብት ጥናት አተገባበር ፕሮግራም ላይ እንደተመለከተው ከግድብና ከመስኖ ልማት ጋር ተያይዞ በአጠቃላይ 3,443 አባወራዎች ወይም 17,655 ግለሰቦች ከአካባቢው እንደሚነሱ ተገልጿል፡፡

115. የከሰም ተንዳሆ ፕሮጀክት የካሳ ክፍያ የ2001ዓ.ም የስራ ሂደት ሪፖርት ላይ ፕሮጀክቱ የተጀመረው በ1997ዓ.ም ሲሆን በፕሮጀክቱ የስራ ሂደት የመሬት ይዞታቸውን ለሚለቁ ሰዎች የፕሮጀክቱ ስራ ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ ካሳ ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባ እንደነበር ተገልጿል፡፡ነገር ግን የፕሮጀክቱ ስራ እንዲጀመር ከነበረው አጣዳፊነት አንጻር የካሳ ክፍያው የጥናት ስራ እና የኮንስትራክሽን ስራው አንድ ላይ ተጣምረው እንዲጀመሩ መደረጉን፣ ፕሮጀክቱ ሲጀመር ይነሳ የነበረውን ከፍተኛ የካሳ ክፍያ ጥያቄ መመለስ እንዳልተቻለ በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡

116. የካሳ ክፍያው ቁጥሩ ከፍተኛ ከሆነ ህዝብ (17,655) ጋር የተገናኘ እንደመሆኑ መጠን የካሳ ክፍያ ጥናትም ሰፊ እና ጊዜ የሚፈልግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የፕሮጀክቱ ስራ ከመጀመሩ በፊትም ነዋሪዎች ስፍራውን መልቀቅ ያለባቸው መሆኑ እየታወቀ የጥናት ስራው በቅድሚያ እንዲከናወን አለመደረጉ አግባብነት ያለው አሰራር ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በተደረገው የጥድፊያ ካሳ ክፍያ ፕሮጀክቱን አስፈላጊ ላልሆነ ተጨማሪ ክፍያ የዳረገው፣ ከህብረተሰቡም ጋር ያለመግባባት እንዲፈጠር ያደረገ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

117. በ2000 ዓ.ም በተዘጋጁ የፕሮጀክት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶች (Office memorandums) ላይ እንደተገለጸው የተወሰኑ ገበሬዎች ለካሳ ክፍያ የእርሻ መሬታቸውን በሚያስለኩበት ወቅት ቀያሾች (ሰርቬየሮችን) በማስገደድ ታርሶ የማያውቀውንም መሬት ጨምረው በማስለካታቸው እንደገና ማጣራት ተደርጎ ቀደም ሲል በውሀ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ተለክቶ የተወሰነው ከክፍያ ውጪ እንዲሆን የተደረገበት ሁኔታ እንደነበር ታውቋል፡፡

118. የፕሮጀክቱ ግንባታ ስራ በተጀመረበት ወቅት ለባለይዞታዎቹ ተገቢው ካሳ ተከፍሏቸው ስፍራውን ለስራ ነጻ ማድረግ አስፈላጊ የነበረ ቢሆንም ተግባራዊ ባለመደረጉ ከህብረተሰቡ ጋር ያለመግባባት በመኖሩ የተለያዩ ችግሮች ሊከሰቱ ችለዋል፡፡ ለመጥቀስ ያህል ሥራ እንዳይሰራ ማስቆም፣ የተሰሩ ስራዎችን ማበላሸት፣ ስራ ማከናወኛ ንብረቶችን መስረቅ እንዲሁም፣ በስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ላይ የዘረፋና የድብደባ ችግር እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘጋጁ ሪፖርቶች ተገልጿል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባለይዞታዎቹ ከቦታቸው ሲለቁ ተለዋጭ ቦታ ሊዘጋጅላቸው የሚገባ በመሆኑና ይህ ባለመከናወኑ ከተከፈላቸው ካሳ ተጨማሪ ተለዋጭ ቦታ እስኪሰጣቸው ድረስ ተጨማሪ ክፍያ ይከፈላቸው እንደነበረ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም ሁኔታ ፕሮጀክቱን ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ ይሆናል፡፡

119. ይህንንም በተመለከተ በኦዲት የመውጫ ስብሰባው ወቅት ከስራ ኃላፊዎቹ ጋር በተደረገው ውይይት ለሚፈናቀለው የአካባቢው ህብረተሰብ የካሣ ክፍያው በቅድሚያ እንዲከፈል ያልተደረገው እንደዚህ ዓይነት ችግር ይከሰታል የሚል ግምት ስላልነበር መሆኑን ተገልጿል፡፡

<u>***የግንባታ ስራ ዕቃዎች መጠባበቂያ ክምችት* (Stock) *መያዝን በተመለከተ***</u>

120. የፕሮጀክቱ ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚያስፈልጉ የግንባታ ስራ እቃዎች አቅርቦት አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ጥናት ሊደረግበት ሲገባ ተግባራዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠንተው በቅድሚያ እንዲዘጋጁ አለመደረጋቸው ሥራው በእቅዱ መሰረት እንዳይሄድ አድርጓል፡፡ በሥራ ተቋራጩ በኩል የግንባታ ዕቃ አቅርቦትና የመጠባባቂያ ክምችት ቅድመ ዝግጅት ባለመደረጉ በየጊዜው በገበያ ላይ የነበረውን የእቃ አቅርቦት ችግር ለመቋቋምም ሆነ የተለያዩ አማራጮችን ለመፈለግ ከፍተኛ ችግር እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

121. ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ1999ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ በአማካሪ ድርጅቱ በቀረቡ ሪፖርቶች ላይ በተደጋጋሚ ለስራው መጓተት ምክንያት ተብሎ የሚገለጸው ችግር የስራ ተቋራጩ አቅም ማነስና የግንባታ እቃዎች እጥረት መሆኑ ተመልክቷል፡፡

122. ይህንንም በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ በስራ ተቋራጩ አቅም ማነስ ምክንያት ፕሮጀክቱ ሲጀመር በቂ የመጠባበቂያ ክምችት አለመያዙን ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ ይህ የሲሚንቶ፣ የብረት፣ የኮንስትራክሽን መኪናዎችና መለዋወጫዎች (spare parts) በአገሪቷ የተከሰቱ ችግሮች እንደነበሩም አብራርተዋል፡፡

123. በከሰም የፕሮጀክቱ የስራ ተቋራጭ ድርጅት ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጋጥማቸው የሲሚንቶ እጥረት ችግር እንደነበረና ሌሎች የግንባታ እቃዎችን በብዛት ገዝቶ ለማከማቸት የአቅም እጥረት እንደነበረ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በተንዳሆ ለስራ ተቋራጩ ድርጅት ኃላፊ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በገንዘብ እጥረት ምክንያት በመስኖ ልማቱ ግንባታ ስራ ላይ ከፍተኛ የሆነ የማሽንና የነዳጅ እጥረት በተደጋጋሚ ተከስቶ እንደነበርም ገልጸዋል፡፡

124. ፕሮጀክቱ ከፍተኛ የሆነ የግንባታ ዕቃዎች የሚያስፈልጉት ሆኖ ሳለ የአቅርቦቱንና በየደረጃው ለሚከናወኑ ግንባታዎች የመጠባበቂያ ክምችት ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የዚህ አይነቱ አካሄድ በአቅርቦት ችግር ምክንያት ሥራ የማቆም፣ ተጨማሪ ወጪ የሚያስከትልና ቀድመው የተሠሩ ሥራዎችን ለብልሽትና ጉዳት የሚዳርግ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

125. በመውጫ ስብሰባው ወቅት የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልግ ክምችት (Stock) ከፍተኛ ገንዘብ የሚይዝበት በመሆኑ ለሥራ ተቋራጩ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆን፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለምሳሌ የሲሚንቶ እጥረት ችግር እየፈጠረ ሲመጣ በቅድሚያ በመክፈል አቅርቦቱ እንዳይቋረጥ የማድረግ ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል፡፡

<u>ከመስኖ ልማቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ስለሚሰሩ የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ በተመለከተ</u>

126. ለፕሮጀክቱ ስራ መጓተት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት ችግሮች መካከል አንዱ ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር የተፈጠረው አለመግባባት እንደሆነ በሥራ ሪፖርቶች ተገልጿል፡፡ ይህንንም ችግር በዋነኝነት ከሚያባብሱት ምክንያቶች አንዱ ማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከልና ለአካባቢው ነዋሪዎች እንዲውል የታቀደው የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ቅድሚያ ተሰጥቶት ባለመገንባቱ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ከመስኖ ልማቱ መሬት ዝግጅት ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የታቀደው የልማት ሥራ (የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ) ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊገነባ ይገባል፡፡

127. ከአፋር ክልል የፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ካሳ ተከፍሏቸው ከፕሮጀክቱ ስፍራ እንዲለቁ ለተደረጉ ነዋሪዎች የግጦሽ እና የእርሻ መሬት እንዲሁም የመኖሪያ ቤቶች በተገባው ግዴታ መሰረት እንዳልተዘጋጀላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በሚሌ አካባቢ በ2000ዓ.ም (ከአንድ ዓመት በፊት) ከፕሮጀክቱ ስፍራ የለቀቁ ነዋሪዎች እነዚህ ሁኔታዎች ያልተሟሉላቸው መሆኑና የመጠጥ እና ለመስኖ የሚሆን የውሀ አቅርቦት ያልተመቻቸ መሆኑን ከተደረገው ቃለ ምልልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

### <u>የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ዝግጅትን በተመለከተ</u>

128. የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ (project proposal) ለማንኛውም ፕሮጀክት የመነሻ ሀሳብ መግለጫና ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያካትት በመሆኑ ለወደፊት ለሚዘጋጁ ፕሮጀክቶች ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልበት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

### <u>የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናትን (Feasibility study) በተመለከተ</u>

129. አንድ የፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ በእጅ ያለውን ሀብት እና ተጨማሪ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች (ገንዘብ፣ ጊዜ፣ አደረጃጀትና የገበያ ሁኔታ፣ ወ.ዘ.ተ...) በመለየት ስራው ቢሰራ ካለው ወቅታዊ ሁኔታ እና የወደፊቱን ከግምት በማስገባት አዋጭ መሆኑ በቅድሚያ እንዲጠና መደረግ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ለወደፊት ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት እንዲጠና መደረግ ይኖርበታል፡፡

### <u>የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ  ጥናትን በተመለከተ</u>

130. የግድብና መስኖ ልማት ግንባታ ስራ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልገው መሆኑ በአገሪቷ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (Environemental impact assessement) አዋጅ የተደነገገ ነው፡፡ በመሆኑም የግድብና መስኖ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ ፕሮጀክቱ በአካባቢው ላይ የሚያስከትለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ተጽእኖና ጠቀሜታ መለየትና በምን አይነት መንገድ በስራ ላይ መዋል እንደሚገባቸው በቅድሚያ መጠናት አለበት፡፡

### <u>የፕሮጀክቱን ስራ እንዲከታተልና እንዲያስተባብር ስለተቋቋመው ጽ/ቤት</u>

131. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ስር የሚገኘው የከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በተፈቀደው ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት በሰው

ኃይል እንዲሚላና ሀላፊነቱን በሙሉ አቅሙ እንዲያከናውን አስቸኳይ መፍትሄ ሊደረግለት ይገባል፡፡ በተጨማሪም ጽ/ቤቱ ኃላፊነቱና የስራ ድርሻው በጽሁፍ ሊዘጋጅለት እና ለፅህፈት ቤቱ ኃላፊ (ተጠሪ) እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡ ለጽ/ቤቱ ሰራተኞችም የስራ ድርሻ መዘርዝር በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዳቸው እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

## <u>የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያን በተመለከተ</u>

132. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮጀክቱን የሥራ አፈጻጸም ሂደት ለመከታተል፣ለመቆጣጠርና በየደረጃው የተከናወኑ ስራዎች በትክክል እየተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ወጥነትና ተቀባይነት ባለው መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የስራ አመራር መመሪያ ማዘጋጀትና ተፈፃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## <u>በፕሮጀክት ስራ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን (Risks) በተመለከተ</u>

133. ማንኛውም ፕሮጀክት በስራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶች ስለሚኖሩት በቅድሚያ ተጠንተውና ተለይተው በፕሮጀክቱ የስራ እቅድ ውስጥ እንዲካተቱ መደረግ አለበት፡፡ይህ መደረጉ ችግሮች እንዳይከሰቱ የመከላከያ ዘዴዎችን በቅድሚያ ለመንደፍ፤ በስራ ወቅት በሚከሰቱ ችግሮች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድ እና ከአቅም በላይ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችም በሌሎች የውጭ አካሎች የሚከናወኑበት(የሚተዳደሩበት) አሊያም እንደአስፈላጊነቱ የመድን ዋስትና እንዲኖራቸው ለማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ሊታመንበትና ለወደፊት ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አሰራር ሊመቻች ይገባል፡፡

## <u>የመስኖ ልማት ግንባታ ዲዛይኖች ዝግጅትን በተመለከተ</u>

134. ማንኛውም የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ ዲዛይን ሊዘጋጅለት፣በሞያተኛ ሊገመገም፣ ባለድርሻ አካላት አስተያየት ሊሰጡበት እና በበላይ ኃላፊዎች ተቀባይነት እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡

## <u>የግንባታ ሥራው ወርሃዊ አፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅትን በተመለከተ</u>

135. ማንኛውንም የፕሮጀክት የስራ አፈጻጸም አስመልክቶ የስራ ክንውን ሪፖርት በየወሩ እየተዘጋጀ እና በተቆጣጣሪው (በአማካሪው) አካል ትክክለኛነቱ እየተረጋገጠ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርብበት ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ የሚዘጋጀው የስራ

አፈፃፀም ሪፖርት ወጥነት ያለው፣ በእቅድ የተያዘውን እና ክንውኑን በግልጽ በማሳየትና በማመዛዘን ለሥራ አመራሩ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

## <u>በመስኖ ግንባታ ስራ ላይ የሚሳተፉ የተቋራጭና የአማካሪ ባለሙያዎችን መረጃ ማቅረብን በተመለከተ</u>

136. የውሀ ሀብት ሚኒስቴር ከተቋራጭና አማካሪ ድርጅቶች ጋር ስምምነት አድርጎባቸው የሚከናወኑ የፕሮጀክት ስራዎች ላይ የተሰማሩ የተቋራጭ እና የአማካሪ ድርጅቶች ባለሙያዎችን ዝርዝር ሁኔታ አውቆ ሥራውን ለመስራት ብቃት ያላቸው መሆናቸውን በየጊዜው መገምገምና ማጽደቅ አለበት፡፡ በመሆኑም ተቋራጩ እና አማካሪ ድርጅቶች በየጊዜው በስራው ላይ የሚመድቧቸውን ባለሙያዎች ዝርዝር በየወሩ ለፕሮጀክቱ ባለቤት በሪፖርት በቅድሚያ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡ የከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራም ይህን አሰራር ስርዓት እንዲከተል መደረግ አለበት፡፡

## <u>የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ የመስኖ መሬቶች ርክክብን በተመለከተ</u>

137. የውሀ ሀብት ሚኒስቴር እና የስራ ተቋራጩ ባደረጉት ስምምነት ላይ በተገለጸው ውል መሰረት ስራቸው የተጠናቀቀ የመስኖ መሬቶች ርክክብ መደረግ ያለበት በስራ ተቋራጩ ድርጅት እና በፕሮጀክቱ ባለቤት መካከል በመሆኑ በውሉ መሰረት ርክክቡ እንዲፈፀም መደረግ አለበት፡፡ለርክክቡም የመረካከቢያ ቅፅ (ፎርማት) ተዘጋጅቶ በሰነድነት ሊያዝ ይገባል፡፡

## <u>የግንባታ ስራቸው ለተጠናቀቁ የመስኖ መሬቶች መደረግ ያለበትን ጥበቃ በተመለከተ</u>

138. የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ የመስኖ መሬቶች ከፕሮጀክቱ ባለቤት ጋር ርክክብ እስከሚደረግባቸው ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳት ሊደርስባቸው እና ተጨማሪ ወጪ ሊያስከትል ስለሚችል የስራ ተቋራጭ ድርጅቱ አስፈላጊውን ጥበቃ ሊያደርግ ይገባል፡፡ መሬቶቹም ለጉዳት ያልተጋለጡና በአግባቡ እየተጠበቁ ለመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኘው የፕሮጀክቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ክትትል ሊያደርግበትና ስለሁኔታው ለበላይ አካል በሪፖርት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## የፕሮጀክቱን መሪ እቅድ (Master plan) በተመለከተ

139. ለማንኛውም ፕሮጀክት የሚዘጋጅ መሪ እቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡የሚዘጋጀው መሪ ዕቅድም በየስንት ጊዜው መከለስ እንዳለበት የጊዜ ገደብ ሊኖረው ይገባል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአፋር ክልል ከተቋቋመው የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት በተመለከተ

140. በአፋር ብሔራዊ ክልል የተቋቋመው የከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማት ኘሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሊያከናውነው ስለሚገባው ዝርዝር ተግባር የስራ ድርሻና ኃላፊነት በፅሁፍ ተዘጋጅቶና ውይይት ተደርጎበት ለጽ/ቤቱ እንዲደርስ መደረግ ይኖርበታል፡፡ጽ/ቤቱም ኃላፊነቱን ለመወጣት በሰው ኃይል ሊሟላ፣ በእቅድ ሊመራና የስራ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ የሚችልበት አሰራር እንዲመቻችለት መደረግ አለበት፡፡

## የግንባታ ስራ ዕቃዎች መጠባባቂያ ክምችት (stock) በተመለከተ

141. ማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ በግንባታ ዕቃዎች እጥረት ምክንያት ስራው እንዳይስተጓጎል የሥራ ተቋራጩ በቂ የግንባታ ዕቃ በመጠባበቂያነት (stock) ሊይዝ ይገባል፡፡በተጨማሪም የተለያዩ አማራጮችን (ከእቃ አቅራቢዎች ጋር ውለታ መግባትን፣የአገር ውስጥ ምርቶችን በቅድሚያ ለማግኘት እንዲያስችል ድጋፍ የመጠየቅን፣ከውጭ የማስገባትን፣ወዘተ) የማጥናትና አስተማማኝ ሁኔታ መኖሩን የኮንትራት ውል ከመፈፀሙ በፊት የሚረጋገጥበት አሰራር መኖሩ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ይረዳል፡፡

## ለተሰሩ ስራዎች የሚፈፀሙ ክፍያዎች በወቅቱ መከናወኑን በተመለከተ

142. የፕሮጀክቱ ባለቤት ከስራ ተቋራጩ የሚቀርቡለት የክፍያ ጥያቄዎች በውሉ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት እንዲከፈል ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው፡፡ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ የክፍያ መጠየቂያ ሰነዶች በአማካሪ ድርጅቱ እጅ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚቆይበት ቀናት የጊዜ ገደብ ሊቀመጥላቸው ይገባል፡፡

## የመስኖ ልማቱ ፕሮጀክት በሚሰራበት አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ስለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግን በተመለከተ

143. በመስኖ ልማቱ አካባቢ ሰፍሮ የሚገኘው ሕብረተሰብ የመስኖ ልማቱ ባለድርሻ አካል እንደመሆኑ መጠን በቅድሚያ መስኖ ልማቱ ለአካባቢው መሻሻልና ለነዋሪዎቹ ስለሚኖረው ጠቀሜታ በአካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡

## በመስኖ ልማቱ ግንባታ ምክንያት ከይዞታቸው ለሚፈናቀሉ የአካባቢው ኗሪዎች ስለሚከፈለው ካሣ /Compensation/ በተመለከተ

144. የፕሮጀክቱ ስራ ከሚሰራበት ቦታ ላይ ለተነሱ ባለይዞታዎች በህጉ መሰረት በመንግስት የተፈቀደው የካሳ ክፍያ በቅድሚያ ሊከፈላቸው ይገባል፡፡ ለወደፊቱ በሚሰሩ ተመሳሳይ የፕሮጀክት ስራዎች ላይ ለስራው የሚፈለገውን ቦታ አስቀድሞ በማጥናት ለቦታው ባለይዞታዎች ተመጣጣኝ ካሳ በመክፈል አካባቢውን ለስራው ነጻ የማድረጉ ሥራ የፕሮጀክቱ ስራ ክንውን ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊከናወን ይገባዋል፡፡

## ከመስኖ ልማቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ስለሚሰሩ የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ በተመለከተ

145. ከመስኖ ልማቱ መሬት ዝግጅት ጋር በተያያዘ እየተከሰቱ ላሉ ማህበራዊ ችግሮች አንዱ መንስኤ ካሳ ተከፍሏቸው ከቦታው እንዲለቁ ለተደረጉ ነዋሪዎች የግጦሽ መሬት፣ የመኖሪያ ቤቶችና ሌሎች አስፈላጊ የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ በተገባው ቃል መሰረት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊገነባ ይገባል፡፡ በስራ ሂደቱም ከህብረተሰቡ ጋር በየጊዜው የምክክር መድረክ በማዘጋጀት የመተማመንና የመግባባት ደረጃ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ ስራዎች በተጓዳኝ ሊከናወኑ ይገባል፡፡

146. በመጨረሻም በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በሥራ ተቋራጩ ድርጅት፣ በአማካሪ ድርጅቱ፣ በፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ እና በሌሎች በኦዲቱ የታዩ ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት በኦዲቱ ወቅት ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

<u>የኦዲት መስፈርት መመዘኛዎች</u>

<u>(Evaluative criteria)</u>

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት፡- <u>የውኃ ኃብት ልማት ሚ/ር</u>

<u>የከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት (Irrigation) ፕሮጀክት</u>

<u>እና በፕሮጀክት ስራው የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት</u>

ያዘጋጀው <u>መሐሪ ተከስተ</u>

የከለሰው <u>አለማየሁ ተክሉ</u>

ያፀደቀው <u>ሠናይት መለሠ</u>

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| 1. | የመስኖ ልማቱ ኘሮጀክት ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ተደርጐ የተጀመረ መሆኑና ኘሮጀክቱ በተያያዘለት ዕቅድ መሠረት መከናወኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ ማረጋገጥ፡፡ | |
| 1.1 | የኘሮጀክቱ ግንባታ ከመጀመሩ አስቀድሞ ተገቢው ቅድመ ዝግጅት የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ | 1.1.1 የፕሮጀክቱ በተለይም የመስኖ ልማቱ ግንባታ ከመጀመሩ አስቀድሞ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ (Project Proposal) ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው ከፍተኛ ኃላፊዎች መጽደቅ አለበት |
| | | 1.1.2 የመስኖ ልማቱ ግንባታ ከመጀመሩ አስቀድሞ ግንባታው በአካባቢው ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖና ጠቀሜታ ተጠንቶና ተለይቶ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተንዳኝ መ/ቤቶች አስተያየት ተሰጥቶበት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
| --- | --- | --- |
| | | ተቀባይነት ማግኘትና መጽደቅ አለበት፡፡ |
| | | 1.1.3 ሚ/ር መ/ቤቱ በፕሮጀክቱ ግንባታ ከሚሳተፉ ድርጅቶች ጋር ሕጉን የተከተለ የግንባታና የአማካሪነት ውል መፈራረም አለበት፡፡ በውሉ ላይም የግንባታ ሥራው የሚጀመርበት እና የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ የመሥኖ መሬት ዝግጅት የሚመደበው የገንዘብ መጠን በውሉ ላይ ሊገለጽ እና በውል ፈፃሚዎች መካከል በጋራ መፈረም አለበት፡፡<br><br>የውል ሠጪ እና ተቀባይ ግዴታዎችም በዝርዝር መገለጽ አለባቸው፡፡ |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ<br><br>(Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች<br><br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | 1.1.4 የኘሮጀክቱን ሥራ የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠውና በኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ስር የሚገኘው የከሠም ተንዳሆ መሥኖ ልማት ኘሮጀክት ክትትል ቡድን ለኘሮጀክቱ በተፈቀደው መዋቅር መሠረት በሰው ኃይል መደራጀት አለበት። |
| | | 1.1.5 ሚ/ር መ/ቤቱ የመስኖ ልማት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመገምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ (Project management manual) አዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ አለበት። |
| | | 1.1.6 መ/ቤቱ በመስኖ ልማት ግንባታው ሒደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን (Risks) በማጥናትና በመለየት ሥጋቶቹ የሚወገዱበት፣ የሚቀነሱበት ወይም ወደ ሌላ አካል የሚተላለፉበት (Risk minimization or risk shifting) አማራጮች ማጥናትና ማዘጋጀት ይኖርበታል። |
| | | 1.1.7 የመስኖ ልማቱን ግንባታ አስመልክቶ የአካባቢው ተስማሚነት፣ የግንባታ ማቴሪያሎች ፍላጐትና አቅርቦት፣ የማህበራዊ ጉዳዮች፣ የእርሻ መሳሪያዎች ፍላጐት፣ የስኳር አገዳ ሁኔታ (Sugar cane development)፣ እና አጠቃላይ የተቋሙ ሁኔታ ትንታኔ በዝርዝር በአማካሪ መሐንዲሱ ተጠንቶ ለፕሮጀክቱ ባለቤት ሊቀርብለትና ሊስማማበት ይገባል። ሚ/ር መ/ቤቱም በዚሁ መሠረት አፈፃፀሙን ክትትል ማድረግና እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። |
| | | 1.1.8 ለስኳር አገዳ (commercial sugarcane) የሚሆነው የመስኖ ልማት መሬት ከመዘጋጀቱ እና በአገዳ ከመሸፈኑ አስቀድሞ የአካባቢው አፈር ለስኳር አገዳው ተስማሚ መሆኑ የመስኖ ልማት ኘሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት በአፈር |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ<br><br>(Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች<br><br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | ምርመራ (soil test) መረጋገጥ አለበት፡፡ በምርመራ ያረጋገጠው አካልም ይህን አስመልክቶ ማረጋገጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | | 1.1.9 በአማካሪ መሐንዲሱ የሚዘጋጅ የመስኖ ልማቱ የግንባታ ዲዛይኖች በወቅታዊ የአካባቢው የመሬት ሁኔታ (Topography) ላይ የተመሰረቱ፣ ተደጋጋሚ የዲዛይን ለውጥ የማያስከትሉ እንዲሆኑ፣ ዲዛይኑ ስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ በቂ ጥናት እንዲደረግበት በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል ለአማካሪ መሐንዲሱ ተገቢው መመሪያ ሊሰጥ ይገባል፡፡ የዲዛይን ጥናትም ተቀባይነት ለማግኘቱ በኃላፊዎች በፊርማ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | | 1.1.10 ሚ/ር መ/ቤቱ በኘሮጀክቱ አካባቢ (site) የራሱን ስራተኞች በመመደብ ከቀጠረው አማካሪ መሀንዲስ ክህሎት እንዲቀስሙና (Skill Transfer) ወደፊት ሚ/ር መ/ቤቱ ለሚያከናውኗቸው ተመሳሳይ የግንባታ ስራዎች እንደ In house consultancy የሚያገለግሉት ሠራተኞች ማዘጋጀት ይገባዋል፡፡ |
| | | 1.1.11 የመኖ ልማት ኘሮጀክቱ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት በግንባታው ላይ የሚሳተፉ አጋር ድርጅቶች ማንነት ያለባቸው የሥራ ድርሻና ኃላፊነት መለየትና እንዲስማሙበት መደረግ ይኖርበታል፡፡ |
| 1.2 | ሚ/ር መ/ቤቱ ኘሮጀክቱ በተያዘለት ዕቅድ መሠረት መከናወኑን ለመቆጣጠር፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ | 1.2.1 የፕሮጀክቱን ሥራ እንዲመሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው የውሀ ህብት ልማት ሚ/ር እና የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር መ/ቤቶች በየሁለት ወሩ እየተገናኙ የመስኖ ልማት የግንባታ ሂደቱን መገምገም ይኖርባቸዋል፡፡ በግንኙነታቸው ወቅት የሚተላለፉ ውሳኔዎች እና በወቅቱ የተነሱ ጉዳዮችም በስርዓቱ በቃለ-ጉባዔ ሊያዙና ሊጠበቁ ይገባል፡፡ የተሠጡ ውሣኔዎችም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ<br><br>(Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች<br><br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | መበተን (መድረስ) አለበት፡፡ |
| | | 1.2.2 በየወሩ በሥራ ተቋራጩ (contractor) እየተዘጋጀ በአማካሪ መሐንዲሱ አማካኝነት ለፕሮጀክቱ ባለቤት በሚላኩ የስራ ሪፖርቶች ላይ<br><br>- ለወሩ በዕቅድ የተያዘው (Planned) እና በሥራ ላይ የዋለው (Actual) የሰው ኃይልና ማሽኖች፣ ለዕቅድ የሚያስፈልግ የግንባታ ማቴሪያል፣<br>- ወቅታዊ የሥራ ፕሮግራም እንዲሁም ለዋጋ ልዩነት የተከፈሉ ተጨማሪ የVariation ጥያቄዎች ሊያካትት ይገባል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱም በሪፖርቱ መሠረት ተገቢው እርምጃ እና ማስተካከያ በወቅቱ በመውሰድ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | | 1.2.3 አማካሪ መሐንዲሱ የመስኖ ልማቱን በተመለከተ የገባውን ግዴታ ለመወጣት ይችል ዘንድ በመስኖ ልማቱ ስራ አገልግሎት እንዲሰጡ የመደባቸውን ሠራተኞች ዝርዝር ሁኔታ (Biographical data) የሚገልጽ ሰነድ በማዘጋጀት ለፕሮጀክቱ ባለቤት ማሳወቅ አለበት፡፡ የፕሮጀክቱ ባለቤትም በውሉ ላይ በተገለፁት 15 ቀናት ውስጥ ስምምነቱን ወይም ተቃውሞውን መግለጽ አለበት፡፡ ቀደም ብለው በፕሮጀክቱ ላይ በተመደቡ የሰው ኃይልና መሠረት ሥራው ለመሠራቱም ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 1.2.4 ደረጃ በደረጃ በተጠናቀቀ የመስኖ ልማት መሬቶች አቅርቦትና ርክክብ (Provisional and final Acceptance) መፈፀም ያለበት ከፕሮጀክቱ ባለቤት (ውሃ ሐብት ሚ/ር) ጋር መሆን ይኖርበታል፡፡<br><br>በርክክብ ወቅትም መሟላት የሚገባቸው ፎርሞች ሁሉ በደንቡ መሠረት እና ተጠያቂነት በሚያመለክቱ ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ<br><br>(Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች<br><br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | |
| | | 1.2.5 ደረጃ በደረጃ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማቱ የግንባታ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ርክክብ እስኪደረግባቸው ድረስ ለብልሽት እንዳይደረጉ በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ወይም በሌሎች ባለድርሻ አካላት አማካኝነት ተገቢው ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ |
| | | 1.2.6 በስራ ተቋራጩ ተዘጋጅተው እና በአማካሪ መሐንዲሱ ፀድቀው ለፕሮጀክቱ ባለቤት የቀረቡ የክፍያ ጥያቄዎች (payment certificate) በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ መሠረት ለተከናወኑ ሥራዎች መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ክፍያውም በዚሁ መሠረት በወቅቱ መከፈሉ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | | 1.2.7 የተጨማሪ ሥራ ክፍያ (variation cost) ጥያቄ የቀረበው በኘሮጀክት ሰነዱ ላይ በተገለፀው መሠረት በውሉ ላይ ላልተካተቱ ተጨማሪ ሥራዎች መሆኑ፣ ለሚመለከተው አካል ቀርበው ለፀደቁ ሥራዎች ብቻ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በውሉ ለተካተቱ ሥራዎች ሆኖ excess quantity የተጨማሪ ክፍያ እንዳይፈፀም መከታተልና መቆጣጠር አለበት፡፡ |
| | | 1.2.8 በዋናው ውል ተካትተው ለተሰረዙ ስራዎች (omitted works) ተይዞ የነበረው ሂሣብ ከክፍያ መቀነስ አለበት፡፡ ክፍያው ለመቀነሱም የኮንትራት አስተዳደር መምሪያው መቆጣጠርና ለሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡ |
| | | 1.2.9. ለመስኖ ልማቱ ግንባታ በክፍያ መጠየቂያ (Payment certificate) መሠረት ከሚፈፀም ክፍያ በተጨማሪ በሚ/ር መ/ቤቱ በኩልም ሆነ በሌሎች ለመስኖ ልማቱ ግንባታ የሚደረጉ |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ<br><br>(Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች<br><br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | የተለያዩ የዓይነት ዕገዛዎች ማለትም የተሽከርካሪ የሰው ኃይል ወ.ዘ.ተ. በገንዘብ እየተተመነ ከመስኖ ልማቱ አጠቃላይ ወጪ ጋር ሊያዙ ይገባል፡፡ |
| | | 1.2.10 የመስኖ ልማት መሬት ዝግጅት እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች የኘሬጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት በሚያሳየው Master plan “B” መሠረት መከናወን አለበት፡፡ |
| | | 1.2.11 አጠቃላይ የኘሮጀክቱ ግንባታ ስራ በተጀመረ በሁለተኛው ዓመት (ከ1999) ጀምሮ ደረጃ በደረጃ የመስኖ ልማት ወይም የአገዳ እርሻ ልማት መጀመር አለበት፡፡ ለዚህም ሚ/ር በተለይም የኮንትራት አስተዳደር መምሪያው መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 1.2.12 ለመስኖ ልማቱ የተፈፀሙ ክፍያዎች በውሉ መሠረት ተለይተው ሊመዘገቡና ሊያዙ ይገባል፡፡ በውሉ ከተገለፀው በላይ ክፍያ እንዳይፈጸምም የሚ/ር መ/ቤቱ የኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ተገቢው ክትትል ሊደረግ እና ሪፖርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 2. የመስኖ ልማቱ ግንባታ በዕቅዱ መሠረት ተጠናቅቆ ለተያዘለት ዓላማ እንዲውል ለማስቻል የሚ/ር መ/ቤቱ በዋናነት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱ እና ተፈጻሚ መደረጉን ማረጋገጥ፡፡ | 2.1 ሚ/ር መ/ቤቱ በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ስር ከተቋቋመው የኘሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር የሚኖረው የሥራ ግንኙነት በዝርዝር ሊገለጽና ሁለቱም አካሎች ሊስማሙበት ይገባል፡፡ |
| | | 2.2 ሚ/ር መ/ቤቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ ወረዳዎች እና ሌሎች የመስኖ ልማቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በመስኖ ልማቱ አካባቢ ሰፍሮ የሚገኘው ሕብረተሰብ ስለመስኖ ልማቱ ጥቅም በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ሕብረተሰቡን |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | ያሣተፈ የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይት ማድረግ ይኖርበታል፡፡<br><br>በግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይቱ ላይ በተነሱ ነጥቦች ላይ የተደረሱ የመግባቢያ ሐሣቦች በጽሑፍ ተዘጋጅተው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ለባለድርሻ አካላት ሊደርሱ እንዲሁም በሚ/ር መ/ቤቱ በሠነድነት ሊያዙ ይገባል፡፡ የስራ ሂደቱንም በተመለከተም በሚ/ር መ/ቤቱ የካንትራት አስተዳደር መምሪያ በየጊዜው ክትትል እየተደረገ ጉዳዩ ለከፍተኛ ባለስልጣኞች እና ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ |
| | | 2.3 ለመስኖ ልማት በሚዘጋጀው መሬት አካባቢ ሠፍረው ለሚገኙ  እና በዚሁ ግንባታ ምክንያት በኑሮአቸው ለሚፈናቀሉ የአካባቢው ኗሪዎች እንዲከፈል በመንግሥት የተፈቀደው ካሣ /Compensation/ እቅድ ተዘጋጅቶለት በወቅቱ ሊከፈል ይገባል፡፡ |
| | | 2.4 ካሳ የተከፈላቸው የአካባቢ ኗሪዎች የካሣ ክፍያ ከተፈፀመላቸው በኂላ በመሬቱ ላይ ሰብልና የመሳሰሉት ንብረቶች ከሌሉበት በ30 ቀናት፣ ካሉበት ደግሞ በ 90 ቀናት ውስጥ ከቦታቸው መነሳት አለባቸው፡፡ ይህንንም ግዴታ ካሣ የሚከፈላቸው ነዋሪዎች በቅድሚያ እንዲያውቁትና ክፍያውን በሚረከቡበት ወቅት እንዲፈርሙ መደረግ አለበት፡፡ |
| | | 2.5 ለመስኖ ልማት ግንባታ  በሚዘጋጀው ዲዛይን ላይ የመስኖ ልማቱ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች ዲዛይኑ ከመዘጋጀቱ አስቀድሞ አስተያየት እንዲሰጡ መደረግ ይኖርበታል፣ የሚሰጡትን አስተያየት አማካሪ መሐንዲሱ እንደግብዓት (Input) ሊጠቀምበት ይገባል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱም በዚህ በኩል ተገቢው ክትትል ማድረግ አለበት፡፡ |
| | | 2.6 ሚ/ር መ/ቤቱ ለመስኖ ልማቱ ግንባታ ወርሐዊ እና ዓመታዊ የስራ ዕቅድ ሲያዘጋጅ በግንባታ |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ<br><br>(Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች<br><br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | ሒደቱ የሚሳተፍ ባለሙያዎች ወይም ኃላፊዎች (at project level) እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡ መደረግ አለበት፡፡ አስተያየቱም በስራ ዕቅድ ሊካተት ይገባል፡፡ |
| | | 2.7 የመስኖ ልማት መሬት ዝግጅትና ግንባታ በተመለከተ በተለያዩ አካላት የሚዘጋጀው ሪፖርት ተመሳሳይ መረጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም አማካሪ መሐንዲሱ በተዘጋጀው ሪፖርት ትክክለኛነት ላይ አስተያየት በመስጠት ስምምነቱን መግለጽ ይኖርበታል፡፡ |
| | | 2.8 የመስኖ ልማቱ ግንባታ በግንባታ ስራ ዕቃዎች ዕጥረት ምክንያት እንዳይጓተት የሥራ ተቋራጩ በቂ የግንባታ ዕቃ ከነመጠባበቂያው (stock) እንዲያዝ መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም የስራ ተቋራጩ የግንባታ ዕቃዎች እጥረት እንዳይገጥመው የሚ/ር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 2.9 የፕሮጀክቱ ባለቤት ከስራ ተቋራጩ፣ አማካሪ መሐንዲሱ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ለሚቀርቡለትና መፍትሄ ለሚሹ ጉዳዮች አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | | 2.10 የሚ/ር መ/ቤቱ ለስኳር ፋብሪካዎች በየዓመቱ ሊያቀርብላቸው የሚችለውን የመስኖ ልማት መሬት ቀደምብሎ ማሳወቅ አለበት ድርጅቶችም በመስኖ ልማቱ ዙሪያ የሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት (የሰው፣ የማሽን) በተሰጣቸው መረጃ ላይ የተመሰረተ አንዲሆን እና (Idle Machinery Manpower) እንዳያጋጥም ከፋብሪካዎቹ ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | | 2.11 ከመስኖ ልማቱ መሬት ዝግጅት ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት የታቀደው የልማት ሥራ (የመሰረተ ልማት |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | አውታሮች ግንባታ) ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊገነባ ይገባል፡፡<br><br>ሚ/ር መ/ቤቱም አካሄዱ በፕሮጀክቱ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብት ጥናት አተገባበር ፕሮግራም መሰረት መሆኑን መከታተል አለበት፡፡ |
| | | 2.12 ሚ/ር መ/ቤቱ ለመስኖ ልማቱ የተዘጋጀው መሬት leveling ደረጃ ላይ እንደደረሰ በውሉ መሠረት ለስኳር ለፋብሪካዎቹ ማስረከብ አለበት |
| | | 2.13 ከመስኖ ልማቱ ዝግጅት ጋር ተያያዥነት ያላቸውና ጊዜያዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ተብለው የሚከናወኑ የግንባታ ስራዎች ግንባታው የሚጠይቀው ወጪ ከሚያስገኘው ጥቅም ጋር Cost Benefit Analysis እየተሠራ አዋጭነቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ የጊዜያዊ ግንባታው ተጠቃሚዎችም ግንባታው ከመጀመሩ አስቀድሞ አስተያየት እንዲሰጡበትና ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችም በስራው ሂደት እንዲካተት ሊደረግ ይገባል፡፡ |